

# ਨਵੇਂ ਅਤੇ ਵਧ ਰਹੇ ਮਸੀਹੀਆਂ ਲਈ ਮੱਢਲੇ ਬਾਈਬਲ ਅਧਿਐਨ

# ለአዳዲስና በማደግ ላይ ላሉ ክርስቲያኖች የሚሆኑ መሠረታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶች

Copyright © 2022

Charles “Chic” Shaver፣ ደራሲ

**Basic Bible Studies for New and Growing Christians**
**By Charles "Chic" Shaver**
**Copyright © 1972**
**Published by Beacon Hill Press of Kansas City**
**A division of The Foundry Publishing**
**Kansas City, Missouri 64109 USA**
**This edition published by arrangement**
**with The Foundry Publishing.**
**All rights reserved.**

**ለተማሪው መግቢያ**

እርስዎ አሁን ክርስቲያን ሆነዋል። እንደ ክርስቲያን እንዴት ማደግ እንዳለብዎት መማር ያስፈልግዎታል። ክርስቲያናዊ እድገትን በሚመለከት ስምንት ትምህርቶችን ያጠናሉ።

እያንዳንዱን ትምህርት በግልዎ ያጥኑ። መጽሐፍ ቅዱስን ያንብቡ። በተቻለዎ መጠን ጥያቄዎቹን ይመልሱ። ከዚያም፣ ከአስተማሪዎ ወይም ከመጋቢዎ ጋር ይገናኙ። እነርሱ ይረዱዎታል። እርስዎ የማያውቋቸውን ጥያቄዎች ይመልሱልዎታል። እነርሱ ትምህርቶቹን እንዲገነዘቡ ይረዱዎታል።

በእያንዳንዱ ትምህርት ውስጥ በቃል የሚያዝ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ያገኛሉ። እነዚህን ጥቅሶች መማር አለብዎ። ጥቅሶቹን በቃል ይያዟቸው። እነዚህ ጥቅሶች ለክርስቲያናዊ እድገት ይረዱዎታል።

አንዳንድ ጊዜ፣ **ልክ እንደዚህ** በደመቁ ፊደላት የተጻፉ ቃላትን ይመለከታሉ። እነዚህ ቃላት ወይም ሃረጎች ለእርስዎ እንግዳ ሐሳቦች ሊሆኑ ይችላሉ፤ በየትምህርቱ መጨረሻ ላይ የቃላቱን ዝርዝር ከአጫጭር ትርጉሞች ጋር ያገኛሉ።

እግዚአብሔር በጣም ይወድዎታል። የእርስዎ አምላክ መሆን ይፈልጋል። ስለእርሱ እንዲያውቁ ይፈልጋል። እግዚአብሔርን ሊያወሩት ይችላሉ። እርዳታውን ሊጠይቁ ይችላሉ። እንዲገነዘቡ ያደርግዎታል። እንዲማሩ ያደርግዎታል።

**መግቢያ፥ ለአስተማሪው**

አዲስ ክርስቲያን ወደ ጌታ እንደመጣ/ እንደመጣች ወይም በተቻለ ፍጥነት ይህንን መጽሐፍ ይስጡ። አማኙ ትምህርቶቹን እንዲያነብ እና ጥያቄዎቹን በቻለው/በቻለችው አቅም እንዲመልሱ ያበረታቷቸው። በአንድ የጥናት ጊዜ አንዱን ትምህርት ብቻ እንዲሠራ አማኙን ያበረታቱ። በትምህርቱ ላይ ለመወያየት በየሳምንቱ ከተማሪው ጋር የሚገናኙበት ጊዜ ያመቻቹ።

ተማሪው ትምህርቱን በራሱ ማንበብ የማይችል ከሆነ፣ ትምህርቶቹን በጋራ ማንበብ እና መወያየት የምትችሉበትን ጊዜ ያመቻቹ። አንዱን ትምህርት በአንድ ክፍለ ጊዜ መሸፈን የሚመረጥ ቢሆንም፣ ለአንዱ ትምህርት ከአንድ በላይ ክፍለ ጊዜ መውሰድም አስፈላጊ ሆኖ ሊገኝ ይችላል። ተማሪው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን እንዲመለከት ይርዱት። ተማሪው ወደቀጣዩ ትምህርት ከመሄዱ በፊት ምን ያህል እንደተረዳ ለማረጋገጥ ጥያቄዎቹን በጋራ ይስሯቸው።(መልስ ሊሆኑ የሚችሉ፥ በአባሪው ላይ ሊገኙ ይችላሉ።)

**ትምህርት 1**

**ክርስቲያኖች የእግዚአብሔር ናቸው**

***በቃል የሚያዝ ጥቅስ፦***

> ኢየሱስም እንዲህ አለ፣ "እነሆ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ፤ ማንም ድምፄን ቢሰማ ደጁንም ቢከፍትልኝ፥ ወደ እርሱ እገባለሁ"። (የዮሐንስ ራዕይ 3፥20)

ከዚህ ቀጥሎ ላለው ለእያንዳንዱ ጥያቄ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ወይም በአዲስ ኪዳን ውስጥ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ትምህርቶችን ያግኙ። "የዮሐንስ ወንጌል 1፥12" ማለት የዮሐንስ ወንጌል፣ ምዕራፍ 1፣ ቁጥር 12 ማለት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ መጀመሪያ ላይ ያሉትን የመጽሐፍ ዝርዝሮች ይመልከቱ። ለሁሉም መጽሐፎች የገጽ ቁጥሮችን ያገኛሉ። መጽሐፎቹ የሚጀምሩበትን የገጽ ቁጥሮች ያግኙ፡፡ ጥቅሶቹን ከመጽሐፍ ቅዱስ አውጥተው ያንብቡ፡፡ ከዚያም በትምህርቶቹ ውስጥ ያሉትን እያንዳንዱን አረፍተ ነገር እና ጥያቄ ያንብቡ። መልሶቹን በራስዎ አገላለጽ ይጻፉ ወይም ከመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ያሉትን ቃላት ይጠቀሙ። (ብሉይ ኪዳን ውስጥ ያሉ ጥቅሶች ታትመውሎታል።)

1. የዮሐንስ ወንጌል 1፥12 ላይ ያንብቡ። ኢየሱስን **ወደ ልቤ** ተቀብያለሁ። ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር መሆኑን አምናለሁ። ኢየሱስ **አዳኜ** ነው። እኔ **ክርስቲያን** ነኝ። ይህ ማለት የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ማለት ነው? (አዎን ወይም አይደለም)

2. ለተቀበሉት ሁሉ ኢየሱስ ወዳጃቸው ነው። ኢየሱስ **ወደ ልባችን** ሊመጣ ይፈልጋል። ለመምጣት እየጠበቀ ነው። እኛ ግን ልንጋብዘው ይገባናል። የዮሐንስ ራዕይ 3፥20 ላይ ያንብቡ እና ቀጥሎ ያሉትን ጥያቄዎች ይመልሱ።

   ሀ) **ወደ ልባችን** መምጣት የሚፈልገው ማን ነው?

   ለ) ለኢየሱስ ድምጽ ማን ምላሽ መስጠት ይችላል?

   ሐ) ኢየሱስ፡ እኔ ምን እንዳደርግ ይፈልጋል?

   መ) የልቤን በር ስከፍትለት ኢየሱስ ምን ያደርጋል?

   ሠ) ኢየሱስ **ወደ ልብዎ** እንዲመጣ ጠይቀዋል? (አዎን ወይም አይ)

   ረ) አሁን ላይ እርስዎ **ክርስቲያን** ነዎት? (አዎን ወይም አይ)

3. የሉቃስ ወንጌል 19፥20 ላይ ያንብቡ። ኢየሱስ ክርስቶስ የመጣው የጠፉ ሰዎችን ሊያድን ነው? (አዎን ወይም አይ)

| |
|---|
| "የጠፋ" ማለት ኢየሱስን እንደ አዳኝ የማያውቅ ማንኛውም ሰው ነው። |

4. ወደ ሮሜ ሰዎች 3፥23 ላይ ያንብቡ።

   ሀ) ሰዎች ለምን **የጠፋ ሰው** ይሆናሉ?

   ለ) ኃጢአት በመሥራታቸው ምክንያት ነው? (አዎን ወይም አይ)

ሐ) ወደ ሮሜ ሰዎች 6፥23 ላይ **ኀጢአት** "ደመወዝ" አለው ወይም ሞትን ያመጣብናል ሲል ምን ማለቱ ነው?

መ) ይህ ማለት **ኀጢአት፡ ኀጢአተኞችን** ከእግዚአብሔር ያቆራርጣል ማለት ነው? (አዎን ወይም አይ)

| |
|---|
| **ኀጢአተኞች** ሲሞቱ **ሲዖል** ውስጥ ይኖራሉ። ነገር ግን፣ ኢየሱስ ክርስቶስ **ለአማኞች የዘላለም ሕይወት** ስጦታን ሰጥቷቸዋል። **አማኞች** ሲሞቱ **በገነት** ውስጥ ይኖራሉ። |

5. ወደ ሮሜ ሰዎች 5፥8 ላይ ያለውን ያንብቡ። ኀጢአተኞች ሳለን ስለእኛ የሞተው ማን ነው?

6. 1ኛ ዮሐንስ መጽሐፍን ያውጡ። የሚገኘው በአዲስ ኪዳን መጨረሻ አካባቢ ነው። 1ኛ ዮሐንስ ከዮሐንስ ደብዳቤዎች አንዱ ነው። ከዮሐንስ ወንጌል መጽሐፍ ጋር አንድ አይነት አይደለም። 1ኛ ዮሐንስ 1፥9 ላይ ያለውን ያንብቡ። **ኀጢአታችንን** ብንናዘዝ እግዚአብሔር ምን ያደርጋል?

| |
|---|
| **መናዘዝ** ማለት **ኀጢአተኞች እንደሆንን ለእግዚአብሔር** ማመን ማለት ነው። |

7. ትንቢተ ኢሳይያስ 55፥7 እንዲህ ይላል፤ "ክፉ ሰው መንገዱን በደለኛም አሳቡን ይተው።" ቀጥሎ እንዲህ ይላል፤ "ወደ እግዚአብሔርም ይመለስ እርሱም **ይምረዋል።" ስለኀጢአታቸው ንስሐ መግባት** ይገባቸዋል። ቀጥሎ ያሉትን ጥያቄዎች ይመልሱ።

ሀ) ክፉ ሰው መተው የሚገባው ምን ማድረግን ነው?

ለ)በክፉ ሐሳቦቻቸው ላይ ምን ማድረግ አለባቸው?

ሐ) ንስሐ ስንገባ እግዚአብሔር ምን ያደርጋል?

8. ወደ ኤፌሶን ሰዎች 2፥8-9 ላይ ያለውን ያውጡ። ትክክለኛው መልስ ምንድን ነው? (ሀ፣ ለ ወይም ሐ) ለእኔ ወይም ለማንኛውም ሰው **የመዳን** መንገዱ ምንድን ነው?

ሀ. በጣም ብዙ በጎ ሥራ መሥራት ይገባኛል።

ለ. ራሴን **ለማዳን** መሞከር ይገባኛል።

ሐ. እኔን **እንዲያድነኝ** በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ይገባኛል።

9. ኤፌሶን 2፥10 ላይ ያለውን ያንብቡ።

ሀ) ከዳንን በኋላ ምን እናድርግ?

ለ) በጎ ሥራዎቻችን ያድኑናል? (አዎ ወይም አይ)

10. በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ማንን ለማወቅ ነው የምንማረው? (የዮሐንስ ወንጌል 14፥6 እና 14፥9)

11. ፲ኛ ዮሐንስ 5፥13 ላይ ያለውን ያንብቡ። **አማኞች** አሁን ላይ **የዘላለም ሕይወት** እንዳላቸው ማወቅ ይችላሉ? (አዎ ወይም አይ)

12. የዮሐንስ ወንጌል 6፥47 ላይ ያለውን ያንብቡ።

   ሀ. በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምን ሰው **የዘላለም ሕይወት** አለው? (አዎ ወይም አይ)

   ለ. ይህ ማለት ለዘላለም እኖራለሁ ማለት ነው? (አዎ ወይም አይ)

   ሐ. ስሞት የምኖረው የት ነው?

13. እርስዎ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆኑ ያውቃሉ? አዎ ካሉ፣ እንዴት እንዳወቁ በራስዎ አገላለጽ ሊናገሩ ይችላሉ?

| |
|---|
| ኢየሱስ አዲስ ሕይወት ሰጥቶዎታል። እርስዎ የእግዚአብሔር ልጅ ነዎት። አሁን፣ እንደ ክርስቲያን እንዴት ሊያድጉ ይችላሉ? እነዚህ የተሰወኑ አስፈላጊ የእድገት መንገዶች ናቸው፡፡ |

*መጽሐፍ ቅዱስን በየእለቱ ያንብቡ።* የማቴዎስ ወንጌል 4፥4 ላይ ያለውን ያንብቡ። ከዚያም፣ ከዮሐንስ ወንጌል መጽሐፍ ላይ አንድ ምዕራፍ በየእለቱ ያንብቡ። እነዚህ ትምህርቶች፡ ከዮሐንስ ወንጌል እና ከሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የተውጣጡ ጥያቄዎች አሏቸው። በእያንዳንዱ ትምህርት ያለውን በቃል የሚያዝ ጥቅስ ያጥኑት። እያንዳንዱን ጥቅስ በቃልዎ ያስታውሱ።

| |
|---|
| *በየእለቱ ይጸልዩ።* ከእግዚአብሔር ጋር ይነጋገሩ። የተከሸኑ ቃላትን መናገር አይጠበቅብዎትም። ከልብ ወዳጅዎ ጋር እንደሚያወሩት ከእግዚአብሔር ጋር ያውሩ።<br><br>*በተቻለዎ መጠን ወደ ቤተክርስቲያን ይሂዱ።* መጽሐፍ ቅዱስን ወደሚያስተምር ቤተክርስቲያን ይሂዱ። ስለኢየሱስ ወደሚሰብክ ቤተክርስቲያን ይሂዱ። ከሌሎች **ክርስቲያኖች** ጋር አብረው መሆን ያስፈልግዎታል። ለኢየሱስ እንዲኖሩ ይረዱዎታል።<br><br>*እግዚአብሔርን ይታዘዙ።* እግዚአብሔር እንዲረዳዎ ይጠይቁ። ምን ማድረግ እንደሚገባዎ ይነግርዎታል። በመጽሐፍ ቅዱስ  በኩል ይናገርዎታል። በቤተክርስቲያን ውስጥ ይናገርዎታል። ምን ማድረግ እንዳለብዎ ግራ ሲገባዎ፣ ራስዎን እንዲህ ብለው ይጠይቁ፡ “ኢየሱስ ቢሆን ምን ያደርግ ነበር?” ምላሽዎ እግዚአብሔርን እንዲታዘዙ ይረዳዎታል።<br><br>*ለሌሎች ሰዎች ይመስክሩ።* ኢየሱስ ክርስቶስ ለእርስዎ ምን እንዳደረገልዎ ይናገሩ። ለሌሎች ሰዎች **ክርስቲያን** መሆንዎን **ይመስክሩ**። |

አሁን፣ **ክርስቲያን** ምን እንደሆነ የተሻለ ግንዛቤ አለዎት። ይህ **የክርስትና** ሕይወትዎ ጅማሮ ብቻ ነው። ገና የሚቀጥል የበለጠ ሐሴት አለ!

*የቃል ዝርዝር*

1. **አማኞች** *(ስም):* ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ **አዳኝ** የሚያምኑ ሰዎች፤ ኢየሱስን **ወደ ልባቸው** የተቀበሉ ሰዎች፤ **ክርስቲያኖች** የሆኑ ሰዎች ሁሉ ናቸው።

2. **ክርስቲያን** *(ተውላጠ ስም):* **ከኀጢአቱ ንስሐ የገባ** እና በኢየሱስ *ያመነ*፤ ኢየሱስ ክርስቶስን የሚከተል እና የሚታዘዝ ሰው ማለት ነው።

3. **መናዘዝ** *(ግስ)*: **ኀጢአተኝነትዎን** እንደሚያውቁ ለእግዚአብሔር መናገር፤ ስለ **ኀጢአትዎ** እንዲሁም ስለ ክፉ ሐሳቦችዎ እና ተግባሮችዎ ለእግዚአብሔር መናገር።

4. **የዘላለም ሕይወት** *(ስማዊ ሐረግ):* እግዚአብሔር የሚሰጠው ሕይወት፤ ከእግዚአብሔር ጋር አሁን ላይ እና **በገነት** ለዘላለም የሚኖር ሕይወት።

5. **ይቅር ማለት** *(ግስ):* ለክፉ ሐሳቦቹ እና ተግባሮቹ አንድን ሰው ሳጠይቀጡ መተው፤ (**ንስሐ ስንገባ** እግዚአብሔር **ኀጢአታችንን ይቅር ይለናል** እንዲሁም ይረሳዋል።)

6. **ገነት** *(ስም):* ከሞት በኋላ **የክርስቲያኖች** መኖሪያ።

7. **ሲኦል** *(ስም):* ከሞት በኋላ **ኀጢአተኞች** የሚቀጡበት ስፍራ።

8. **ወደ ልቤ፣ ወደ ልባችን** *(ቅድመ-ውሳኔ ሐረግ):* ወደ ውስጠኛው የሰው ክፍል፤ በሰዎች መካከል፤ (ልብ የሚያካትተው አዕምሮን፣ ፈቃድን እና የሰውን ፍላጎቶች ነው።)

9. **መጥፋት** *(ቅጽል):* የእግዚአብሔርን መንገድ አለማግኘት፤ያለ**ዘላለም ሕይወት** ተስፋ መሆን፤ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ **አዳኝ** አለማወቅ።

10. **ንስሐ መግባት** *(ግስ):* እግዚአብሔር **ኀጢአትን ይቅር እንዲል** መጠየቅ፤ **ከኀጢአት** ተመልሶ ፊትን ወደ እግዚአብሔር ማዞር።

11. **ማዳን፤ ያድናል** *(ግስ):* **ከኀጢአት** ነጻ ማድረግ፤ (ኢየሱስ ክርስቶስ ከኀጢአታችን **ያድነናል** ወይም **ከኀጢአታችን** ያነጻናል። ስለዚህ፣ **ሲኦል** ውስጥ ከመቀጣት **ያድነናል**።)

12. **አዳኝ** *(ተውላጠ ስም):* ኢየሱስ ክርስቶስ፤ እኛን **ከኀጢአት ያዳነን** ማንነት።

13. **ኀጢአት መሥራት***(ግስ):* **ኀጢአቶች***(ስም):* ክፉ *ሥራዎችን መሥራት* እና ክፉ ሐሳቦችን ማሰብ፤ እግዚአብሔርን አለመታዘዝ፤ መጥፎ ሐሳቦች ወይም ተግባራት።

14. **ኀጢአተኛ** *(ስም):* የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የማያከብር ሰው፤ **ኀጢአት የሚሠራ** ሰው።

15. **መመስከር** *(ግስ):* ለሰዎች ስለኢየሱስ ክርስቶስ መናገር፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ለእርስዎ ያደረገልዎትን መናገር።

**ትምህርት 2**

**ክርስቲያኖች ከእግዚአብሔር ጋር ይሔዳሉ**

***በቃል የሚያዝ ጥቅስ፥***

> “ለሰው ሁሉ ከሚሆነው በቀር ምንም ፈተና አልደረሰባችሁም፤ ነገር ግን ከሚቻላችሁ መጠን ይልቅ ትፈተኑ ዘንድ የማይፈቅድ እግዚአብሔር የታመነ ነው፡” (1ኛ ቆሮንቶስ 10፥13)።

አዳዲስ ክርስቲያኖች በአንዳንድ ሁኔታዎች እንደ ህጻናት ናቸው። ህጻናት ከተወለዱ በኋላ ያድጋሉ። ክርስቲያኖች እንደ አዲስ አማኝ በኢየሱስ ማደግ ይገባቸዋል። ክርስቲያኖች በእግዚያብሔር ሲታመኑ ያድጋሉ። ክርስቲያኖች እግዚአብሔርን ሲታዘዙ ያድጋሉ። እድገታችንን፡ “ከእግዚአብሔር ጋር መሔድ” ብለን እንጠራዋለን። ሚክያስ እንዲህ አለ፣ “ከአምላክህም ጋር በትሕትና ትሄድ ዘንድ..” (ትንቢተ ሚክያስ 6፥8)። ሚክያስ በብሉይ  ኪዳን ጊዜ የነበረ ነቢይ ነው።

የሚከተሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች አውጥተው ያንቡቧቸው። ከዚያም ጥያቄዎቹን በራስዎ አገላለጽ ይመልሷቸው። ወይም፣ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ቃላት ይጠቀሙ።

1. የዮሐንስ ወንጌል መጽሐፍ ከእግዚአብሔር ጋር እንዴት እንደምንሔድ ይነግረናል።

   ሀ. የዮሐንስ ወንጌል 8፥12 ላይ ያለውን ያንብቡ። ክርስቲያኖች በጨለማ ውስጥ ይኖራሉ ወይም ይራመዳሉ? (አዎን ወይም አይ)

   ለ. እግዚአብሔር ሕይወት በሚሰጠው ብርሃን ውስጥ እንድንራመድ ይፈልጋል? (አዎ ወይም አይ)

   ሐ. የዮሐንስ ወንጌል 1፥37 ላይ ያለውን ያንብቡ። ክርስቲያኖች መከተል የሚገባቸው ማንን ነው?

   መ. የዮሐንስ ወንጌል 2፥5 ላይ ያለውን ያንብቡ። ክርስቲያኖች ኢየሱስ ያዘዛቸውን ነገር በሙሉ ማድረግ ይገባቸዋል? (አዎ ወይም  አይ)

   ሠ. የዮሐንስ ወንጌል 5፥14 ላይ ያለውን ያንብቡ። ክርስቲያኖች ለእግዚአብሔር አለመታዘዛቸውን ማቆም አለባቸው?

2. 1ኛ ጴጥሮስ 5፥8 ላይ ያለውን ያንብቡ። ከእግዚአብሔር ጋር እንድንራመድ የማይፈልገው ማን ነው?

3. የማቴዎስ ወንጌል 4፥1 ላይ ያለውን ያንብቡ። **ዲያብሎስ** ኢየሱስ ላይ ምን አደረገ?

4. ዕብራዊያን 4፥14-15 ላይ ያለውን ያንብቡ። መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ **ተፈተነ** ብሎ ይነግረናል። ኢየሱስ **ለፈተና ተሸንፏል?** (አዎ ወይም አይ)

| |
|---|
| **ፈተና** እና ኀጢአት አንድ አይነት ነገሮች አይደሉም። **ፈተና** ማለት ልክ ያልሆነ ነገር እንዲያደርጉ መመራት ወይም መጋበዝ ነው። ኀጢአት ልክ ያልሆነ ነገርን መሥራት ማለት ነው። **ፈተና** ኀጢአት ነው? (አዎ ወይም አይ) |

5. **ዲያብሎስ ሲፈትነን** ወደ እግዚአብሔር መጸለይ አለብን። **ዲያብሎስን** በእግዚአብሔር እርዳታ እንገጥመዋለን። ያዕቆብ 4፥7 ላይ ያለውን ያንብቡ። **ዲያብሎስ ሲፈታተንዎ** ምን ማድረግ ይኖርብዎታል?

6. ያዕቆብ 4፥17 እና 1ኛ ዮሐንስ 3፥4 ላይ ያለውን ያንብቡ። ኀጢአት ምንድን ነው?

7. ትንቢተ ኢሳይያስ 59፥2 እንዲህ ይላል፣ "ነገር ግን በደላችሁ በእናንተና በአምላካችሁ መካከል ለይታለች፥" ኀጢአቴ እኔን ከእግዚአብሔር ለይቶኛል? (አዎ ወይም አይ)

8. 1ኛ ዮሐንስ 3፥9 ላይ ያለውን ያንብቡ።

   ሀ. ይህን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ እርስዎ እንዴት ይረዱታል?

   ለ. የእግዚአብሔር ልጅ የሆነ ሰው ኀጢአት መሥራቱን ይቀጥላል?

9. 1ኛ ቆሮንቶስ 10፥13 ላይ ያለውን ያንብቡ። እግዚአብሔር ለእኛ ቃል የገባው ነገር ምንድን ነው? (ሀ ወይም ለ)

   ሀ. እግዚአብሔር **ከፈተና** እንዳመልጥ ይረዳኛል። **በፈተና እንዳልወድቅ** ይረዳኛል።

   ለ. እግዚአብሔር **ከፈተና** እንዳመልጥ አይረዳኝም። **በምፈተንበት** ጊዜ አይረዳኝም።

10. 1ኛ ዮሐንስ 2፥1 ላይ ዮሐንስ ይህንን መጽሐፍ እንደጻፈ ይናገራል። ዮሐንስ ይህንን መጽሐፍ ለምን ጻፈ?

11. 1ኛ ዮሐንስ 2፥1 ላይ ያለውን ደግመው ያንብቡ። ክርስቲያኖች ኀጢአት መሥራት የለባቸውም። ለዚህ ጥያቄ የበለጠ ተስማሚው መልስ (ሀ፣ ለ፣ ሐ ወይም መ) የትኛው ነው? ክርስቲያኖች ኀጢአት ለማድረግ ከመረጡ፣ እነርሱ፡

   ሀ. ኀጢአት ከማድረግ መቆጠብ እንደማይችሉ መናገር አለባቸው። ዲያብሎስ ለኀጢአት እንደገፋፋቸው መናገር አለባቸው።

   ለ. ምንም ኀጢአት እንዳልሠሩ ሆነው ማስመሰል አለባቸው።

   ሐ. ኀጢአታቸውን ለኢየሱስ ተናዘው ንስሐ መግባት አለባቸው። ከዚያም ለእግዚአብሔር ለመኖር መቀጠል አለባቸው።

   መ. የክርስትና ሕይወትን መኖር ማቆም አለባቸው። ለኢየሱስ መኖር እንደማይቻላቸው ሊሰማቸው ይገባል።

12. 1ኛ ዮሐንስ 1፥9 ላይ ያለውን ያንብቡ። እግዚአብሔር ኀጢአት እንድንሠራ አይፈልግም፤ ነገር ግን፣ ኀጢአት ብንሠራ ይቅር ይለናል? (አዎ ወይም አይ)

| |
|---|
| ኀጢአታችንን ስንናዘዝ እና ንስሐ ስንገባ ይቅር ይለናል። |

13. የዮሐንስ ወንጌል 14፥21 ላይ ያለውን ያንብቡ። ኢየሱስን ስንታዘዘው ምን እያሳየነው ነው?

14. የዮሐንስ ወንጌል 10፥27-28 ላይ ያለውን ያንብቡ። በዚህ ጥቅስ ውስጥ "በጎቼ" ማለቱ ክርስቲያኖችን ለማመልከት ነው። የዘላለም ሕይወት ያለው ማን ነው?

| |
|---|
| ኢየሱስ ስለበጎቹ ግድ የሚለው መልካም እረኛ ነው። ኢየሱስ ክርስቲያን የሆነውን ሰው ሁሉ ያውቀዋል፡፡ኢየሱስን መከተል ለክርስቲያኖች አስፈላጊ ነው? (አዎ ወይም አይ) |

እንግዲህ ከእግዚአብሔር ጋር ይሒዱ። **በፈተና አይሸነፉ**። እግዚአብሔርን ይታዘዙ። በየቀኑ ኢየሱስ ክርስቶስን ይከተሉ።

*የቃል ዝርዝር*

1. **ዲያብሎስ***(ስም)፡* ሰዎች ልክ ያልሆነ ነገር እንዲያደርጉ **የሚፈታተናቸው** እርኩስ መንፈስ፤ የክፉት ጥግ የሆነው መንፈስ፤ (**ዲያብሎስ** ከእግዚአብሔር ጋር ይጣላል።)
2. **ነቢይ** *(ስም)*፡ ለእግዚአብሔር የሚናገር ሰው፤ (አንድ **ነቢይ** ከእግዚአብሔር የሆነ መልዕክት ለሰዎች ይነግራል።)
3. **መጽናት** *(ግስ)፡* **በፈተና** አለመሸነፍ፤ (በዚህ ጥቅስ **መጽናት** ማለት በእግዚአብሔር መጠንከር ማለት ነው። **መጽናት** ማለት በእግዚአብሔር ላይ ኀጢአት አለመሥራት ማለት ነው።)
4. **መፈተን፣ ተፈተነ** *(ግስ)፡* ሰው ኀጢአት እንዲሠራ ወይም ትክክል ያልሆነ ነገር እንዲያደርግ ለማድረግ መገፋፋት።
5. **ፈተና፣ ፈተናዎች** *(ስም)*፡ አንድ ሰው ኀጢአት እንዲሠራ ወይም ትክክል ያልሆነ ነገር እንዲያደርግ የሚጋብዝ ወይም የሚመራ ማንኛውም ነገር፤ **በዲያብሎስ የመፈተን** ሁኔታ፤ **ዲያብሎስ** አንድን ሰው ኀጢአት እንዲያደርግ ሲገፋፋው።
6. **መተማመን** *(ግስ)፡* በእግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ ማመን፤ በእምነት መሆን፤ ሙሉ በሙሉ ማመን።
7. **እጅ መስጠት** *(ግስ)፡* መማረክ፤ ለኀጢአት "እሺ" ማለት፤ ማድረግ የሌለብንን ነገር ማድረግ።

**ትምህርት 3**

**ክርስቲያኖች ከእግዚአብሔር ይማራሉ**

***በቃል የሚያዝ ጥቅስ፦***

“አንተን እንዳልበድል፥ **ቃልህን በልቤ ሰወርሁ።**” (መዝሙር 119፥11)

መጽሐፍ ቅዱስ **የእግዚአብሔር ቃል ነው።** ቃሉ እግዚአብሔር በሕይወታችን ያለውን እቅድ ይነግረናል። እግዚአብሔር ለአለም ያለውን እቅድ ይነግረናል። የእግዚአብሔርን እውነት ለመረዳት መጽሐፍ ቅዱስን በየዕለቱ ያንብቡ። የእግዚአብሔርን ለእኛ ያለውን ቃል ኪዳን ለመማር መጽሐፍ ቅዱስን ያንብቡ።

የሚከተለውን በራስዎ አገላለጽ ይመልሱ። ወይም፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ውስጥ ያሉ ቃላትን ይጠቀሙ።

1. የዮሐንስ ወንጌል 17፥17 ላይ ያለውን ያንብቡ። **የእግዚአብሔር ቃል** እውነት ነው?

| |
|---|
| **የእግዚአብሔር ቃል** እኛን ያስተምረናል። |

2. 2ኛ ጢሞቴዎስ 3፥16 ላይ ያለውን ያንብቡ። **የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል** የእግዚአብሔር እውነት መሆኑን እንዴት እናውቃለን?

| |
|---|
| ሁሉም **የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል** የእግዚአብሔር እስትንፋስ አለበት ወይም ምንጩ እግዚአብሔር ነው። ከእግዚአብሔር የመጣ ነው ማለት ነው። እግዚአብሔር ሰዎችን እየመራቸው ነው መጽሐፍ ቅዱስን ያስጻፋቸው፡፡ |

3. በሚከተሉት ጥቅሶች ውስጥ **የእግዚአብሔር ቃል** ወይም **የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል** ለእኛ ምን ፋይዳ እንዳላቸው ይናገሩ።

   ሀ. 2ኛ ጢሞቴዎስ 3፥15 ላይ ያለውን ያንብቡ። **የእግዚአብሔር ቃል** ለደህንነት የሚበጀንን የምናውቅ ያደርገናል? (አዎ/አይ)

   ለ. የዮሐንስ ወንጌል 15፥3 ላይ ያለውን ያንብቡ። **የእግዚአብሔር ቃል** የልብ ንጽህናን ይሠጠናል? (አዎ ወይም አይ)

   ሐ. የሐዋርያት ሥራ 20፥32 ላይ ያለውን ያንብቡ። **የእግዚአብሔር ቃል** ጥንካሬን ይሰጠናል? (አዎ ወይም አይ)

4. **የእግዚአብሔር ቃል** ለክርስቲያኖች በጣም አስፈላጊ ነገር ነው። የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 8 ላይ ያለውን ያግኙ። በርካታ ጥቅሶች **በእግዚአብሔር ቃል** ምን ማድረግ እንዳለብን ይነግሩናል።

   ሀ. የዮሐንስ ወንጌል 8፥54-55 ላይ ያለውን ያንብቡ። ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር አብን ያውቃል። ኢየሱስ በእግዚአብሔር ቃል ምን ያደርግ ነበር?

   ለ. የዮሐንስ ወንጌል 8፥37 ላይ ያለውን ያንብቡ። አንዳንድ ሰዎች የኢየሱስን ትምህርት አይቀበሉም። ለቃሉ ምንም አይነት ቦታ የላቸውም። ይህ ማለት **የእግዚአብሔርን ቃል** አይጠብቁም ማለት ነው? (አዎ ወይም አይ)

ሐ. የዮሐንስ ወንጌል 8፥47 ላይ ያለውን ያንብቡ። አማኝ የእግዚአብሔር ነው እንጂ የዲያብሎስ አይደለም። አማኞች ስለ **እግዚአብሔር ቃል** ምን ያደርጋሉ?

መ. አማኞች እግዚአብሔር ምን እንደሚል ያደምጣሉ? (አዎ ወይም አይ)

ሠ. የዮሐንስ ወንጌል 8፥31 ላይ ያለውን ያንብቡ። አንድ ደቀ መዝሙር **በእግዚአብሔር ቃል** ምን ያደርጋል?

ረ. ደቀ መዛሙርት **የእግዚአብሔርን ቃል** ይታዘዛሉ? (አዎ ወይም አይ)

ሰ. የዮሐንስ ወንጌል 8፥51 ላይ ያለውን ያንብቡ። የዘላለም ሕይወት እንዴት ሊኖረን ይችላል?

ሸ. **የእግዚአብሔርን ቃል** መታዘዝ አስፈላጊ ነገር ነው? (አዎ ወይም አይ)

ኢየሱስ፡ አባቱን እግዚአብሔርን እንደታዘዘ ተናግሯል። ኢየሱስ **የእግዚአብሔርን ቃል** አክብሯል። እኛም እንደዚሁ እግዚአብሔር አባታችንን ማክበር አለብን።

5. የዮሐንስ ወንጌል 14፥23 ላይ ያለውን ያንብቡ። ለኢየሱስን ትምህርቶች ስታዘዝ ለኢየሱስ ምንን አሳየዋለሁ?

6. የዮሐንስ ወንጌል 20፥31 ላይ ያለውን ያንብቡ።

   ሀ. የተጻፈው **የእግዚአብሔር ቃል** የእግዚአብሔር ልጅ ስለሆነው ስለኢየሱስ ይነግረናል? (አዎ ወይም አይ)

   ለ. ኢየሱስ ክርስቶስ ለአማኙ ምን ይሰጣል?

7. ኤፌሶን 6፥17 ላይ ያለውን ያንብቡ። ዲያብሎስ በክርስትና ሕይወታችን ሊያሸንፈን ይጥራል። ይፈትነናል እንዲሁም ኀጢአት እንድንሠራ ያባብለናል።

   ሀ. ዲያብሎስን ለማሸነፍ ምን ልንጠቀም እንችላለን?

   ለ. የመንፈስ ሰይፍ ምንድን ነው?

8. የማቴዎስ ወንጌል 4፥4፣ 4፥7 እና 4፥10 ላይ ያለውን ያንብቡ።

   ሀ. ኢየሱስ ለዲያብሎስ ምን ምላሽ ሰጥቶት ነበር?

   ለ. ኢየሱስ ለምን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ተጠቀመ?

9. መዝሙር 119፥10-11 ላይ ያለውን ያንብቡ።

   ሀ. መጽሐፍ ቅዱስ ኀጢአት እንዳይሠሩ እንዴት ይረዳዎታል?

   ለ. **የእግዚአብሔርን ቃል** ወደ ልባችን ማድረስ ለምን ያስፈልገናል ?

10. **በመጽሐፍ ቅዱስ ቃል** ውስጥ የትኛው እውነት ረድቶዎታል?

11. *መጽሐፍ ቅዱስ በክርስትና ሕይወትዎ እንዲያድጉ ረድቶዎታል?* (አዎ ወይም አይ)

| ምላሽዎ "አዎ" ከሆነ፣ ይህ እውነት ምን እንደሆነ በራስዎ መንገድ ሊገልጹ ይችላሉ? |
| --- |

12. የኢየሱስ **ደቀ መዝሙር** *መጽሐፍ ቅዱስን በየእለቱ ማንበብ እና ማጥናት አለበት። ለምን እንደሆነ በራስዎ አገላለጽ መናገር ይችላሉ?*

ክርስቲያን ከእግዚአብሔር እንዴት እንደሚማር አጥንተናል። *መጽሐፍ ቅዱስ* **ለደቀ መዛሙርት** *ያለውን አስፈላጊነት ተምረናል። በሚቀጥለው ትምህርት፣ ክርስቲያኖች የሚያድጉበት ሌላ ወሳኝ መንገድ እንማራለን።*

*የቃል ዝርዝር*

1. **ደቀ መዝሙር** *(ስም)፡* አማኝ፤ ኢየሱስ ክርስቶስን የሚከተል ሰው፤ ስለኢየሱስ ይበልጥ ለማወቅ የሚፈልግ ሰው፤ **የእግዚአብሔርን ቃል** ማጥናት የሚፈልግ ሰው።

2. **የእግዚአብሔር እስትንፋስ ያለበት** *(ቅጽል)*፡ ከእግዚአብሔር የመጣ።

3. **የእግዚአብሔር ቃል**፡(**የእግዚአብሔር ቃል** የሚለውን ይመልከቱ።)

4. **የተመራ** *(ቅጽል)*፡ ከእግዚአብሔር የመጣ፤ ሃሳብን መስጠት፤ (እግዚአብሔር ቃሉን እንዲጽፉ **መራቸው**)

5. **የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል** *(ተውላጠ ስም)፡* መጽሐፍ ቅዱስ፤ የእግዚአብሔር ቃል፤ (እግዚአብሔር ቅዱሳን ሰዎችን የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል እንዲጽፉ እረዳቸው።)

6. **ቃልህን ወደ ልብ ማድረስ** *(የግስ ሐረግ)፦* የእግዚአብሔርን ቃል ማመን እና መከተል፤ እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ ምን እንደተናገረ መማር እና መረዳት።

7. **የእግዚአብሔር ቃል** *(የተውላጠ ስም ሐረግ)፡* መጽሐፍ ቅዱስ፤ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል፤ የእግዚአብሔር እውነት፤ እግዚአብሔር ለሰዎች የሚናገራቸው ነገር።

## ትምህርት 4

## ክርስቲያኖች ከእግዚአብሔር ጋር ያወራሉ

***በቃል የሚያዝ ጥቅስ፦***

> ኢየሱስም እንዲህ አለ፣ “እስከ አሁን በስሜ ምንም አልለመናችሁም፤ ደስታችሁ ፍጹም እንዲሆን ለምኑ ትቀበሉማላችሁ።” (የዮሐንስ ወንጌል 16፥24)

ክርስቲያኖች ከእግዚአብሔር ጋር ማውራት ያስፈልጋቸዋል። እርሱ በሰማይም ይሁን በምድር ከማንም በላይ ታላቅ ነው። ከእርሱ ጋር በየእለቱ ማውራት አለብን። በእያንዳንዱ ቀን አመቺ ነው በምንለው ጊዜ መጸለይ አለብን። ለብዙ ሰዎች የማለዳው ጊዜ ይበልጥ ይመቻቸዋል። ከእግዚአብሔር ጋር ጸጥ ባለ ቦታ ላይ ማውራት አለብን። በርካታ መዝሙሮችን የጻፈው ዳዊት እንዲህ አለ፣ “በማለዳ ድምፄን ትሰማለህ፥ በማለዳ በፊትህ እቆማለሁ፥ እጠብቃለሁም።” (መዝሙር 5፥3)

መጽሐፍ ቅዱስ ስለጸሎት ሌላ የሚነግረን ምን አለ? የዚህን ምላሽ በዚህ ትምህርት ውስጥ እንማራለን። የሚከተሉትን ጥያቄዎች በራስዎ አገላለጽ ይመልሱ፤ ወይም ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ቃላትን ይጠቀሙ።

1. የማርቆስ ወንጌል 1፥35 ላይ ያለውን ያንብቡ። ኢየሱስ የጸለየው ምን ጊዜ ነበር?

2. ሉቃስ 18፥1 ላይ ያለውን ያንብቡ። ኢየሱስ መቼ መቼ መጸለይ እንዳለብን ተናገረ?

3. 1ኛ ተሰሎንቄ 5፥17-18 ላይ ያለውን ያንብቡ። ስንጸልይ ምን ማድረግ አለብን?

| |
|---|
| በኢየሱስ ክርስቶስ ስላደረገልን ነገር እግዚአብሔርን እናመሰግናለን። |

4. “በልቤስ በደልን አይቼ ብሆን ጌታ አይሰማኝም ነበር።” (መዝሙር 66፥18)

   ሀ. አንዳንድ ጊዜ ጸሎት ለምን ምላሽ አያገኝም?

   ለ. ኀጢአትን በልቤ መያዝ አለብኝ? (አዎ ወይም አይ)

5. 1ኛ ዮሐንስ 5፥14 ላይ ያለውን ያንብቡ።

   ሀ. ይህ ጥቅስ እንዴት መጸለይ እንዳለብን ይነግረናል? (አዎ ወይም አይ)

   ለ. እንዴት መጸለይ አለብን?

| |
|---|
| **የእግዚአብሔር ፈቃድ** የሆኑ ነገሮችን መጠየቅ አለብን። ይህ ለሁሉም ክርስቲያኖች አስፈላጊ ነገር ነው። |

6. በዮሐንስ ወንጌል ላይ ስለጸሎት እንማራለን።

ሀ. የዮሐንስ ወንጌል 16፥24 ላይ ያለውን በቃል የሚያዝ ጥቅስ ያንብቡ። ለክርስቲያኖች የተሰጣቸው **ልዩ መብት** ምንድን ነው?

ለ. ክርስቲያኖች የሚጠይቁትን ሁሉ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም መጠየቅ ይችላሉ? (አዎ ወይም አይ)

| ለማንኛውም፣ ክርስቲያኖች ሁሌም መጸለይ ያለባቸው **የእግዚአብሔር ፈቃድ** ብቻ እንዲፈጸም ነው። |
|---|

ሐ. የዮሐንስ ወንጌል 14፥13 ላይ ያለውን ያንብቡ። ኢየሱስ ጸሎቶቻችንን ይመልሳል። ይህንን የሚያደርግ **ክብርን** ለማን ያመጣል?

| ስለሆነው ነገር ለእግዚአብሔር አብ **ክብር** እንሰጣለን። |
|---|

መ. የዮሐንስ ወንጌል 15፥7 ላይ ያለውን ያንብቡ። ኢየሱስ ጸሎቶቻችንን እንዲመልስ ምን ማድረግ ይገባናል?

| ሁልጊዜም ከኢየሱስ ጋር መኖር መቀጠል ይገባናል። እግዚአብሔር ለእርሱ እንድንኖር ይረዳናል። |
|---|

7. የማቴዎስ ወንጌል 21፥22 ላይ ያለውን ያንብቡ። የጸሎቴን መልስ ለማግኘት ምን ማድረግ ይገባኛል?

| ይህ ማለት በእግዚአብሔር መተማመን ይገባኛል። ጸሎቴን እንዲሰማ በእርሱ እምነት ሊኖረኝ ይገባል። |
|---|

8. እነዚህን ጥቅሶች ያንብቡ እና መጸለይ ስለሚችሏቸው ነገሮች ያስቡ።

- የማቴዎስ ወንጌል 6፥11
- የማቴዎስ ወንጌል 9፥38
- ፊልጵስዩስ 1፥9
- 1ኛ ጢሞቴዎስ 2፥2
- ያዕቆብ 1፥5

9. የማቴዎስ ወንጌል 26፥41 ላይ ያለውን ያንብቡ። በኀጢአት ስፈተን ምን ማድረግ ይገባኛል?

| እግዚአብሔር ኀጢአት እንዳናደርግ ይረዳናል። እንዲረዳን መጠየቅ እንችላለን። |
|---|

10. ኢየሱስ ምን ብለን እንድንጸልይ ይፈልጋል? (ሀ፣ ለ፣ ወይም ሐ) ኢየሱስ እንዲህ እንድናደርግ ይፈልጋል፤

ሀ. ትክክለኛ ሃይማኖታዊ ቃላትን እንድንጠቀም።

ለ. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ ቃላትን ብቻ እንድንናገር።

ሐ. በልባችን ተሰማንን እንድንናገር።

11. ለጸሎት ጊዜዎ መርሐ ግብር አለዎት? (አዎ ወይም አይ)

12. ከእግዚአብሔር ጋር በማውራት ረገድ ምን ማድረግ የሚችሉት ነገር አለ? ለጸሎትዎ ያለዎትን እቅድ በአንድ አርፍተ ነገር ይናገሩ።

| |
|---|
| ጸሎት **ልዩ መብት** ነው! እርስዎ ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር ይችላሉ። እርሱ ጸሎትዎን የመመለስ ብቃት አለው። እግዚአብሔር እርስዎን በጣም ይወድዎታል። በእያንዳንዱ ቀን **ይባርክዎታል**። በብዙ ነገሮች **ይባርክዎታል**። በተለያዩ መንገዶችም እንዲሁ **ይባርክዎታል**። |

አሁን፣ ለእግዚአብሔር አንድ ነገር ማድረግ ይችላሉ። ምን ማድረግ እንደሚችሉ ለመማር የሚቀጥለውን ትምህርት ያጥኑ።

*የቃል ዝርዝር*

1. ***መባረክ*** *(ግስ)፡* መልካም ነገርን መስጠት፤ በልዩ ሁኔታ እርዳታ ማድረግ፤ ማስደሰት።

2. **ክብር** *(ስም)፡* ምስጋና፣ ማሞገስ እና አምልኮ።

3. **ልዩ መብት***(ስም)፡* ልዩ የሆነ ተግባር ወይም *ሥራ፤* (ጸሎት የክርስቲያኖች አንዱ **ልዩ መብት** ነው። ከልብ ጓደኞችን ጋር እንደምናወራው ከእግዚአብሔር ጋር ማውራት እንችላለን። ስለምንፈልጋቸው ነገሮች እግዚአብሔር አብን መጠየቅ እንችላለን። ለዚህም ነው ጸሎት ለክርስቲያኖች ልዩ ተግባር ወይም **ልዩ መብት** የሆነው።)

4. ***ሃይማኖታዊ*** *(ቅጽል)፡* ከሃይማኖት ወይም ከቤተ ክርስቲያን ጋር የተገናኘ አንድ ነገርን ይገልጻል፤ (ስለ ሃይማኖት ወይም ስለቤተ ክርስቲያን ስናወራ ***ሃይማኖታዊ*** ቃላትን እንጠቀማለን።)

5. ***መቆየት****(ግስ)፡* እዚያው መሆን፤ በአንድ ቦታ ላይ መርጋት፤ (በዚህ ጥቅስ ውስጥ፣ መቆየት ማለት በኢየሱስ ክርስቶስ ውስጥ መኖር ማለት ነው። ከክርስቶስ ጋር ለመቆየት እና ትተነው ላለመሄድ መርጠናል።)

6. **የእግዚአብሔር ፈቃድ** *(ስማዊ ሐረግ)፡* እግዚአብሔር ለሁሉም ሰዎች የሚፈልገው ነገር፤ (**የእግዚአብሔር ፈቃድ፡** ፈቃደ እግዚአብሔር ተብሎም ይጠራል።)

**ትምህርት 5**

**ክርስቲያኖች ለእግዚአብሔር ይሰጣሉ**

***በቃል የሚያዝ ጥቅስ፡***

> “እንግዲህ የምትበሉ ወይም የምትጠጡ ብትሆኑ ወይም ማናቸውን ነገር ብታደርጉ ሁሉን ለእግዚአብሔር ክብር አድርጉት።” (1ኛ ቆሮንቶስ 10፥31)

ይህን ጸሎት መጸለይ ይችላሉ?

> *እግዚአብሔር ሆይ፣ በአንተ ከልቤ አምናለሁ። አንተ እንዳዳንከኝ አምናለሁ። በገባኝ መጠን አንተን በይበልጥ በማክበር እኖራለሁ። አንተን ማስደሰት እፈልጋለሁ። አንተን ማገልገል እፈልጋለሁ። ያለኝን ማንኛዉም ነገር ለአንተ **መስጠት** እፈልጋለሁ። እራሴን ለአንተ **መስጠት** እፈልጋለሁ። በኢየሱስ ስም ጸለይኩ። አሜን።*

**ሐዋርያው** ጳውሎስ በቆሮንቶስ ላሉ ክርስቲያኖች ደብዳቤ ጽፎላቸዋል። ሁሉንም ነገር ለእግዚአብሔር ክብር እንዲያደርጉት ነው የነገራቸው። በቃል የሚያዘውን ጥቅስ በድጋሚ ያንብቡት። በምናደርገው ነገር ሁሉ ይህንን ጥያቄ መጠየቅ አለብን፤ ይህ እግዚአብሔርን **ያከብራል**?

1. የማቴዎስ ወንጌል 22፥36-40 ላይ ያለውን ያንብቡ።

   ሀ. እግዚአብሔርን ምን ያህል መውደድ አለብኝ?

   ለ. ባልንጀራዬን ምን ያህል መውደድ አለብኝ?

2. 1ዮሐንስ 5፥2-3 ላይ ያለውን ያንብቡ። ለእግዚአብሔር ፍቅርን የምገልጸው እንዴት ነው? ለሌሎች ሰዎች ፍቅርን የማሳየውስ እንዴት ነው?

3. ዮሐንስ እግዚአብሔር ለማስደሰት ስለመኖር ነግሮናል።

   ሀ. የዮሐንስ ወንጌል 12፥24-25 ላይ ያለውን ያንብቡ። የስንዴ ዘር ብዙ ዘሮችን ከማስገኘቷ በፊት ምን መሆን ይገባታል?

   | |
   |---|
   | ስንዴዋ በአዳዲሶቹ ዘሮች ውስጥ መኖሯን ትቀጥላለች። ለኢየሱስ መኖር አለብኝ። ነገር ግን፣ **ለአለም** መሞት ይገባኛል። **እኔ ከአለም** ፊቴን ማዞር ይገባኛል። **እኔ** እግዚአብሔርን በፍጹም ልቤ መከተል አለብኝ። ኢየሱስ ሕይወትን ሰጥቶኛል። |

   ለ. ኢየሱስን መከተል እና ማገልገል ያለብኝ ለምንድን ነው? (የዮሐንስ ወንጌል 12፥25)

   ሐ. **እራስ ወዳድ** መሆን የለብኝም። ኢየሱስን ለሚያገለግል ለማንኛዉም ሰው እግዚአብሔር አብ ስለሚያደርገው ነገር ኢየሱስ ምን ተናገረ? (የዮሐንስ ወንጌል 12፥26)

4. 2ኛ ቆሮንቶስ 5፥17 ላይ ያለውን ያንብቡ። እኔ አሁን ክርስቲያን ነኝ። ስለማንኛዉም ሰው እና ስለማንኛዉም ነገር አዳዲስ **አመለካከቶች** አሉኝ። አሁን በማን ቤተሰብ ጥላ ስር ነኝ?

| |
|---|
| እኔ የክርስቶስ ነኝ። አሮጌው ማንነቴ ላይመለስ ተሸኝቷል። አሁን፣ በኢየሱስ አዲስ ሰው ነኝ። ነገሮችን የማየው በአዲስ መንገድ ነው። ስለነገሮች አዲስ **አመለካከት** አለኝ። |

5. የሉቃስ ወንጌል 6፥38 ላይ ያለውን ያንብቡ። አሁን፣ የማስወግዳቸው ነገሮች አሉ። ከእኔ ጋር እንዲዘልቅ የማልፈልገው ነገር ምንድን ነው?

6. ሐዋርያው **ጳውሎስ** ስለነገሮች የሚኖረንን **አመለካከት** ጽፎልናል። ኤፌሶን 4፥28 ላይ ያለውን ያንብቡ። ከዚያም፣ ከስር ያለውን ዝርዝር ያንብቡ። ስለነገሮች ሊኖሩን የሚገቡ ሶስት **አመለካከቶችን** ይምረጡ። (ሀ፣ ለ፣ ሐ፣ መ፣ ሠ ወይም ረ)

ሀ. ካሁን በኋላ አለመስረቅ።

ለ. ጥሩ ሠራተኛ መሆን።

ሐ. ሁሉንም ነገር የራሴ ማድረግ። **ራስ ወዳድ** መሆን።

መ. ለድኾችና እና እርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች **ማጋራት**።

ሠ. ሲመቸኝ መስረቅ።

ረ. ሰነፍ መሆን። አለመሥራት።

| |
|---|
| ሰዎችን በአዲስ መንገድ ነው የማያቸው። ስለሌሎች ሰዎች አዲስ **አመለካከት** አለኝ። |

7. ለሌሎች ያለኝን **ርህራሄ** በምን መንገድ ላሳያቸው? (ኤፌሶን 4፥32)

8. 2ኛ ቆሮንስቶስ 6፥14 ላይ ያለውን ያንብቡ። አብሬው መሆን የማይገባኝ ከማን ጋር ነው?

| |
|---|
| እነርሱ ወደ ኀጢአት እንዲመሩኝ መፍቀድ የለብኝም ማለት ነው። እራሴን በአዲስ መንገድ አያለሁ። ስለ እራሴ አዲስ **አመለካከት** ነው ያለኝ። |

9. 1ኛ ቆሮንቶስ 6፥19 ላይ ያለውን ያንብቡ።

ሀ) በእኔ ውስጥ የሚኖረው ማን ነው? ስለዚህ፣ ለሰውነቴ ጥንቃቄ ማድረግ አለብኝ። ሰውነቴን የሚጎዳ ምንም መጥፎ ነገር ማድረግ የለብኝም።

ለ) ተጠንቅቄ የምኖረው ለምንድን ነው?

| |
|---|
| መልካም ነገር ለማድረግ የማገኘውን **እድል** በሙሉ መጠቀም አለብኝ። (ኤፌሶን 5፥15-16) |

10. 1ኛ ዮሐንስ 2፥10 ላይ ያለውን ያንብቡ። የምወደው ማንን ነው?

| |
|---|
| ማለት፡ ሁሉንም ሰዎች መውደድ አለብኝ። "ወንድሜ" የሚለው የሚያጠቃልለው በመሬት ላይ እያንዳንዱን ሰው ነው። |

11. ሁሉንም ሰዎች የፈጠረው እግዚአብሔር ነው። አሁን፣ 1ኛ ዮሐንስ 2፥15-16 ላይ ያለውን ያንብቡ። መውደድ የሌለብኝ ምንድን ነው?

| |
|---|
| **አለማዊ** ነገሮች መውደድ የለብኝም። **ከአለማዊነት** ራሴን ማራቅ ይገባኛል። ከማንኛውም ነገር ይልቅ እግዚአብሔርን መውደድ ይገባኛል። |

12. 1ኛ ቆሮንቶስ 6፥20 ላይ ያለውን ያንብቡ። እግዚአብሔር እርሱን **እንድናከብረው** እና እንድናሞግሰው ለምን ይፈልጋል?

| |
|---|
| እኛ "በዋጋ ተገዝተናል"። "በዋጋ መገዛት" ማለት ኢየሱስ እኛን ከኀጢአታችን ሊያድነን ሞቶልናል ማለት ነው። "ዋጋው" የኢየሱስ ሞት ነው። |

13. የማቴዎስ ወንጌል 6፥33 ላይ ያለውን ያንብቡ።

ሀ) ከሁሉም በላይ ልናየው ወይም ልንፈልገው የሚገባን ነገር ምንድን ነው?

ለ) ሌላስ ምን መፈለግ አለብን?

| |
|---|
| እግዚአብሔር የሚያስፈልገንን ሁሉ ይሰጠናል። |

14. የማርቆስ ወንጌል 10፥29-30 ላይ ያለውን ያንብቡ። ክርስቲያኖች ኢየሱስን የሚከተሉ ናቸው። በቀጣዩ አለም ምን ይቀበላሉ?

15. ሕይወትዎን ለእግዚአብሔር **እንደሚሰጡ** በአንድ አርፍተ ነገር መናገር ይችላሉ?

ሕይወታችንን ለእግዚአብሔር እንዴት **እንደምንሰጥ** አሁን የተሻለ መረዳት አለን። ለሌሎችም ሰዎች ጋር ሕይወታችንን እንዲሁ **መከፋፈል** እንችላለን። ለሌሎች ሰዎች ደግ እና **ሩህሩህ** መሆን አለብን። ይህ እግዚአብሔርን **ያከብራል**። እንዲሁም ስለኢየሱስ ክርስቶስ ለሌሎች ሰዎች መናገር እንችላለን። ስለ ኢየሱስ **ለመናገር** ያገኘነውን እያንዳንዱን **እድል** መጠቀም አለብን። በመቀጠል፣ ኢየሱስን ለሌሎች ሰዎች **ስለመናገር** እንማራለን።

*የቃል ዝርዝር*

1. **ሐዋርያ** *(ተውላጠ ስም)፡* በመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መሪ የሆነ ሰው፤ ልዩ የሆነ የኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዝሙር ወይም ተከታይ።

2. **አመለካከት** *(ስም)፡* ስለ አንድ ነገር ወይም ሰው የሚኖረን ሐሳብ፣ አስተሳሰብ ወይም ስሜት፤ (**አመለካከቶች** ብዙዉን ጊዜ የምናደርገውን ይቆጣጠራሉ።)

3. **ሩህሩህ** *(ቅጽል)፡* ሌሎችን ሰዎች መውደድ እና ለፍላጎታቸው መጨነቅ፤ (ለምሳሌ፣ ክርስቲያኖች የተራቡ ሰዎችን ሲመግቡ፣ **ሩህሩህ** ናቸው።)

4. **ማክበር** *(ግስ)፡* ለአንድ ሰው ክብር፣ ውዳሴ ወይም ሙገሳ ማቅረብ።

5. **እድል** *(ስም)፡* አንድ ነገር የማድረግ መልካም አጋጣሚ።

6. **ጽድቅ** *(ስም)፡* ከኃጢአት መንጻት፤ በእግዚአብሔር ፊት ቅዱስ፣ ጻድቅ እና ትክክል ሆኖ መገኘት።

7. **ራስ ወዳድ** *(ቅጽል)፡* ለራስ ደስታ ብቻ መኖር፤ ከራስ በስተቀር ስለሌሎች ሰዎች ግድ አለመሰኘት።

8. **ማጋራት** *(ግስ)፡* ያለኝን ለሌሎች እና ለእግዚአብሔር መስጠት።

9. **አለም** *(የስም ሐረግ)፡* ኢየሱስ ክርስቶስን ከመከተል የሚከለክለኝ ማንኛውም ወይም የትኛውም ነገር፤ (**አለም** የሚያካትተው ሰውነታችንን የሚጎዱ መጥፎ ልማዶችን ጭምር ነው። የሚያካትተውም ልክ ባልሆነ መንገድ ለማድረግ የሚያበቁን መጥፎ **አመለካከቶችን** ጭምር ነው። ኀጢአት እንድናደርግ የሚፈታተኑንን ሰዎችም ያካትታል። **ዓለም** የሚያካትተው እግዚአብሔርን እንድንረሳ የሚያደርገንን ማንኛዉም ነገር ነው።)

## ትምህርት 6

## ክርስቲያኖች ለእግዚአብሔር ይናገራሉ

***በቃል የሚያዝ ጥቅስ፡***

"እርሱም። በኋላዬ ኑና ሰዎችን አጥማጆች እንድትሆኑ አደርጋችኋለሁ አላቸው።" (የማቴዎስ ወንጌል 4፥19)

አንድ ሰው በጣም የታመመ ጓደኛ ነበረው። በኋላ፣ ሰውየው ጓደኛውን አየው። ጓደኛው ደህና ነበር። "ያዳነኝን ዶክተር አገኘሁት" አለ ጓደኛው። "ስሙ ማን ነው?" ሰውየው ጓደኛውን ጠየቀው። ጓደኛዉም "አልነግርህም" ብሎ መለሰለት። ሰውየውም አዝኖ ሄደ። ወደዚህ ምርጥ ዶክተር እርሱም ለመሄድ ፈልጎ ነበር።

ይህ ታሪክ ብቻ ነው። ግን ታሪኩ ስለአንዳንድ ክርስቲያኖች እንድናስታውስ ያደርገናል። አንዳንድ ጊዜ፣ ክርስቲያኖች ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ለሌሎች አይናገሩም። ኢየሱስ ሁሉንም ሰዎች መርዳት ይችላል። ከኀጢአታቸው ሊያነጻቸው ይችላል። ክርስቲያኖች ስለኢየሱስ ለሌሎች ሰዎች መናገር አለባቸው። ምስክር የሆነ ሰው ኢየሱስ ለእርሱ ወይም ለእርሷ ምን እንዳደረገ ይናገራል ወይም ትናገራለች።

1. የሉቃስ ወንጌል 8፥39 ላይ ያለውን ያንብቡ። ኢየሱስ ክርስቶስ ርኩስ መንፈስ ያለበትን ሰው ፈውሶታል። ይህ ሰው ጥሩ ምስክር ነበር። ከተማውን ሁሉ አዳርሶታል። ሰውየው ስለኢየሱስ ምን ነበር የተናገረው?

2. የዮሐንስ ወንጌል እንዴት እንደምንመሰክር ያስተምረናል። የዮሐንስ ወንጌል 3፥32 ላይ ያለውን ያንብቡ። ከዚያም፣ ትክክለኛውን መልስ ይምረጡ። (ሀ፣ ለ፣ ሐ) መመስከር ወይም መናገር ማለት የሚከተለውን ማጋራት ነው፤

   ሀ) ከመጽሐፎች የተማሯቸውን ነገሮች።

   ለ) አንድ ሰው የነገረንን ነገር።

   ሐ) እራስዎ ያዩት እና የሰሙትን ነገር።

3. የዮሐንስ ወንጌል 1፥40-41 ላይ ያለውን ያንብቡ።

   ሀ) እንድርያስ ወንድሙን አገኘው። የወንድሙ ስም ማን ነበር?

   ለ) እንድሪያስ ለጴጥሮስ እንዲህ አለው "**መሲሁን** አግኝተነዋል።" ወንድሙን ወደ ኢየሱስ የወሰደው ማን ነበር?

| |
|---|
| እንድሪያስ **መስካሪ** ነበር። እርሱ **ሰዎችን አጥማጅ** ነበር። |

4. የዮሐንስ ወንጌል 6፥28-29 ላይ ያለውን ያንብቡ። **በመሲሁ** በኢየሱስ ክርስቶስ ያምናሉ? (አዎ ወይም አይ)

| |
|---|
| ይህ እግዚአብሔር እንድናደርገው የሚፈልገው ነው። ይህ የእግዚአብሔር ሥራ ነው። (የዮሐንስ ወንጌል 6፥28-29) |

5. የዮሐንስ ወንጌል 15፥16 ላይ ያለውን ያንብቡ።

ሀ) እግዚአብሔር ክርስቲያኖች እንዲያፈሩ ወይም እንዲበዛላቸው የሚፈልገው ነገር ምንድን ነው?

ለ) **ፍሬ የምናፈራው** መቼ ነው?

| |
|---|
| **ፍሬ ስናፈራ የሰዎች አጥማጆች** እንሆናለን። |

6. እርስዎ የሰው አጥማጅ መሆን እና ፍሬ ማፍራት ይችላሉ።

ሀ) እርስዎ ላይ የሆነው አስደናቂ ነገር ምንድን ነው?

ለ) መልስዎን በአንድ አርፍተ ነገር መጻፍ ይችላሉ?

ሐ) ስለዚህ ነገር ለሆነ ሰው ተናግረው ያውቃሉ? (አዎ ወይም አይ)

መ) ክርስቲያኖች ለሌሎች ሰዎች እንዴት የበለጠ ደግ መሆን ይችላሉ?

| |
|---|
| ይህ ክርስቲያኖች **ፍሬ ሊያፈሩ** የሚችሉበት አንዱ መንገድ ነው። |

7. የማቴዎስ ወንጌል 28፥18-19 ላይ ያለውን ያንብቡ። ደቀ መዛሙርት እንድናደርጋቸው ኢየሱስ የነገረን ሰዎች እነማን ናቸው?

| |
|---|
| ከዚያም፣ **እናጠምቃቸዋለን። ጥምቀት** የመመስከር አንዱ መንገድ ነው። እኛ ክርስቲያኖች እንደሆንን ለሌሎች ሰዎች **በጥምቀት** እናሳያለን። |

8. የሐዋርያት ሥራ 8፥12 እና 8፥35-38 ላይ ያለውን ያንብቡ።

ሀ) የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች የተጠመቁት መቼ ነበር?

| |
|---|
| ይህ የሚያሳየው **በመሲሁ** በኢየሱስ እንዳመኑ ነበር። |

ለ) ተጠምቀዋል (አዎ ወይም አይ)

ሐ) አይ ካሉ፣ ስለመጠመቅ ያስባሉ? (አዎ ወይም አይ)

9. በቃል የሚያዘውን ጥቅስ ያንብቡ። (የማቴዎስ ወንጌል 4፥19) ኢየሱስ እኛን ምን እንደሚያደርገን ነበር የተናገረው?

10. ለኢየሱስ ምስክር ለመሆን ራሴን ማዘጋጀት አለብኝ። (1ኛ ጴጥሮስ 3፥15) ሁሌም ልሰጥ የማዘጋጀው ነገር ምን መሆን አለበት?

| |
|---|
| ስለእምነቴ ለሚነሱ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ራሴን ማዘጋጀት አለብኝ። ለእግዚአብሔር ለመመስከር ዝግጁ መሆን አለብኝ። |

11. የሐዋርያት ሥራ 17፥16-17 እንዲሁም 20፥20 ላይ ያለውን ያንብቡ። በምኩራብ እና በገበያ ሥፍራ ያሉ ሰዎችን ያገኘው ሐዋርያ የቱ ነው?

| |
|---|
| ዛሬ፣ እርስዎም በማንኛውም ቦታ ምስክር ለመሆን ዝግጁ መሆን ይገባዎታል። |

12. የዮሐንስ ወንጌል 14፥6 ላይ ያለውን ያንብቡ።

ሀ) ስለኢየሱስ ክርስቶስ መመስከር ያለብን ለምንድን ነው?

ለ) ኢየሱስ፡ ማን ነኝ አለ?

| |
|---|
| ማንም ያለኢየሱስ ወደ አብ ሊመጣ አይችልም። ኢየሱስ የዘላለም ሕይወት ልናገኝ የምንችልበት ብቸኛው መንገድ ነው። |

13. ስለኢየሱስ ክርስቶስ መመስከር እችላለሁ። ኢየሱስን ለማያውቅ ሰው ምን ብዬ መናገር አለብኝ? ከስር ካሉት ውስጥ የትኛው መልስ ነው? (ሀ፣ ለ፣ ሐ፣ መ ወይም ሠ)

ሀ. የኀጢአት ደመወዝ ሞት ነው። የእግዚአብሔር ስጦታ ግን የዘላለም ሕይወት ነው። (ሮሜ 6፥23)

ለ. ሰዎች ሁሉ ኀጢአትን ሠርተዋል። (ሮሜ 3፥23)

ሐ. ትንቢተ ኢሳይያስ 53፥6 ላይ እንዲህ ይላል፥ “እኛ ሁላችን እንደ በጎች ተቅበዝብዘን ጠፋን፤ ከእኛ እያንዳንዱ ወደ ገዛ መንገዱ አዘነበለ፤ እግዚአብሔርም የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ አኖረ።” ይህ ማለት ኢየሱስ ለኀጢአታችን በእኛ ቦታ ሞተ ማለት ነው።

መ. **በመሢሁ** ኢየሱስ የሚያምኑ ሰዎች በሙሉ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው። (የዮሐንስ ወንጌል 1፥12)

ሠ. እነዚህን በሙሉ መናገር አለብን (ሁሉም ሀ፣ ለ፣ ሐ እና መ ያስፈልጋሉ)።

14. የሐዋርያት ሥራ 14፥21-22 ላይ ያለውን ያንብቡ።

ሀ. አዳዲስ ክርስቲያኖችን እንዴት መርዳት እንችላለን?

ለ. የበረቱ ክርስቲያኖች እንዲሆኑ ልንረዳቸው እንችላለን? (አዎ ወይም አይ)

ሐ. በእግዚአብሔር ጽኑ እምነት ያላቸው ሰዎች ሆነው እንዲዘልቁ **ማበረታታት** እንችላለን። (አዎ ወይም አይ)

15. የሚመሰክሩት ነገር አለዎት። ክርስቲያኖች **በምስክርነታቸው** ውስጥ ሦስት ነገሮችን ማካተት አለባቸው።

- ክርስቲያን ከመሆኔ በፊት ምን እንደነበርኩ።
- እንዴት ክርስቲያን እንደሆንኩ።

- ኢየሱስ ለእኔ ምን ማለት እንደሆነ።
- ኢየሱስ እንዴት ለእኔ ወዳጄ እንደሆነ።

*ሀ.* ለጓደኛዎ የሚነግሩት አጭር **ምስክርነት** ሊጽፉ ይችላሉ?

ለ. ክርስቲያን ያልሆኑ ሌሎች ሰዎችን ያውቃሉ? (አዎ ወይም አይ)

ሐ. የሦስቱን ሰዎች ስም ሊጽፉ ይችላሉ?

| የቤተሰብዎ አባላት ወይም ጓደኞችዎ ሊሆኑ ይችላሉ። ጎረቤቶችዎ ወይም በሥራ ቦታዎ ያሉ ሰዎች ሊሆኑ ይችላሉ። |
|---|

መ. ለእነዚህ ሰዎች ይጸልዩላቸዋል? (አዎ ወይም አይ)

*ሠ.* ለእነርሱ ይመሰክሩላቸዋል? **ምስክርነትዎን** ይሰጧቸዋል? **ያበረታቷቸዋል**? ጓደኛ ይሆኗቸዋል? (አዎ ወይም አይ)

ሁሉም ክርስቲያኖች ምስክር መሆን እንደሚገባቸው ተምረዋል። ምናልባት ግን፣ እርስዎ **ለመመስከር** ፈርተው ሊሆን ይችላል። ሲፈሩ ማን ሊረዳዎት ይችላል? የመናገር ኃይል ማን ሊሰጥዎ ይችላል? ቀጣዩ ትምህርት እነዚህን ጥያቄዎች ይመልሱልዎታል።

*የቃላት ዝርዝር*

1. **ጥምቀት** *(ስም)፡* ለአዳዲስ ክርስቲያኖች ውሃን በመጠቀም የሚደረግ ልዩ ተግባር ወይም ሥነ ሥርዓት፤ (**ጥምቀት** የሚያሳየው ግለሰቡ በኢየሱስ አዳኝነት እንዳመነ ነው። **በጥምቀት** ግለሰቦቹ በውሃ ውስጥ እንዲጠልቁ ሊስማሙ ይችላሉ። ወይም ውሃ እንዲፈስስባቸው ወይም እንዲረጩ ሊመርጡ ይችላሉ።)
2. **መጠመቅ** *(ግስ)፡* ውሃን በተለየ ተግባር ወይም ሥነ ስርዓት ለአዳዲስ ክርስቲያኖች መጠቀም፤ (**ጥምቀትን** ይመልከቱ።)
3. **ፍሬ ማፍራት** *(የግስ ሐረግ)፡* ኢየሱስን እንደ አዳኝ እንዲያውቁ እና እንዲቀበሉ ሰዎችን መርዳት፤ የኢየሱስ አማኞች እንዲሆኑ ማድረግ ወይም ማብቃት።
4. **ማበረታታት** *(ግስ)፡* በአንድ ሰው ውስጥ ተነሳሽነትን የሚፈጥሩ ቃላትን ወይም ተግባራትን መጠቀም፤ ተስፋ መስጠት፤ አንድን ሰው መርዳት እና መምራት።
5. **የሰዎች አጥማጅ** *(ስማዊ ሐረግ)፡* ለኢየሱስ ክርስቶስ የሚመሰክሩ ክርስቲያኖች፤ ሌሎች ኢየሱስን እንዲያውቁ የሚረዱ ሰዎች።
6. **ለሰዎች አሳ** *(ግሳዊ ሐረግ)፡* ለኢየሱስ ክርስቶስ **ምስክር** መሆን፤ ሌሎች ስለኢየሱስ እንዲያውቁ መርዳት።
7. **መሢህ** *(ተውላጠ ስም)፡* ኢየሱስ ክርስቶስ፤ አዳኝ ለመሆን ወደ ምድር በእግዚአብሔር የተላከው።

8. **ምኩራብ** *(ስም)፡* የአይሁዶች የአምልኮ ቦታ።

9. **ምስክርነት** *(ስም)፡* ኢየሱስ ለሰው ምን እንደሆነ የሚነገሩ ቃላት፤ (ብዙዉን ጊዜ፣ አንድ ግለሰብ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ **ምስክርነት** ይሰጣል።)

10. ***መመ*ስክር** *(ግስ)፡* ኢየሱስ ክርስቶስ ለእርስዎ ያደረገልዎትን መናገር፤ ኢየሱስ አዳኝ እንደሆነ ***መመ*ስክር**።

11. **ምስክር** *(ስም)፡* ኢየሱስ ለእርሱ ምን እንዳደረገለት የሚናገር ሰው።

## ትምህርት 7

## ክርስቲያኖች በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ያስፈልጋቸዋል

***በቃል የሚያዝ ጥቅስ፡***

*"**በመንፈስ** ተሞሉ" (ኤፌሶን 5፥18)።*

ክርስቲያን እንዲህ ሊል ይችላል፥ "ለእግዚአብሔር የበለጠ ለመሥራት እፈልጋለሁ። ነገር ግን፣ ደካማ ነኝ። የበለጠ ኃይል እፈልጋለሁ። ከዚያም፣ ለእግዚአብሔር ብዙ መሥራት እችላለሁ።" ለዚህ መሻት አንድ መልስ ብቻ አለ። ክርስቲያን **በመንፈስ ቅዱስ** መሞላት አለበት። ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ አለ፣ "**በመንፈስ** ተሞሉ።" (ኤፌሶን 5፥18)

1. ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱን አስተምሯቸዋል። ስለ**መንፈስ ቅዱስ** ነግሯቸዋል። ዮሐንስ ኢየሱስ ያስተማራቸውን አንዳንድ ነገሮች ጽፎልናል። የዮሐንስ ወንጌል 7፥38-39 ላይ ያለውን ያንብቡ። ኢየሱስ፡ አንድ ክርስቲያን ማንን ይቀበላል ብሏል?

| |
|---|
| ***መንፈስ ቅዱስ*** *ወደ ክርስቲያን ሕይወት ይመጣል።* |

2. የዮሐንስ ወንጌል 14፥26 ላይ ያለውን ያንብቡ። ማን ያስተምረናል?

| |
|---|
| *መንፈስ ቅዱስ* ***አማካሪ*** *ነው።* ***አማካሪ*** *ማለት እኛን የሚያዳምጠን አካል ማለት ነው። እርሱ ልክ እንደ ረዳት ነው። እርሱ በችግሮቻችን ውስጥ ይረዳናል።* ***መንፈስ ቅዱስ*** *ከእግዚአብሔር የሆነ* ***አማካሪ*** *ነው።* |

3. የዮሐንስ ወንጌል 15፥26 ላይ ያለውን ያንብቡ። ***መንፈስ ቅዱስ*** የእውነት ***መንፈስ*** ነው። ይህ ማለት እርሱ መዋሸት አይችልም ማለት ነው? (አዎ ወይም አይ)

4. እሱ የሚናገረው ስለማን ነው?

| |
|---|
| የዮሐንስ ወንጌል 3፥3-5 ላይ ያለውን ያንብቡ። ***መንፈስ ቅዱስ*** በሰዎች ልብ ውስጥ ይሠራል። እኛ **ዳግመኛ የተወለድን** ስንሆን ከእኛ ጋር አብሮ ይሠራል። ከውሃ እና ከመንፈስ ስንወለድ ከእኛ ጋር ይሠራል። |

5. የሐዋርያት ሥራ 1፥8 ላይ ያለውን ያንብቡ። ***መንፈስ ቅዱስ*** ለደቀ መዛሙርቱ ኃይልን የሰጣቸው ምን እንዲያደርጉበት ነው?

6. የሐዋርያት ሥራ 9፥17 ላይ ያለውን ያንብቡ። ሳውል [ሐዋርያው ጳውሎስ] ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ አዳኝ አድርጎ ተቀብሎታል። ከዚያም፣ ለሳውል "መንፈስ ቅዱስ ይሞላብህ ዘንድ ላከኝ" ብሎ የነገረው ማን ነው?

7. 1ኛ ቆሮንስቶስ 3፥1 እና 3፥3 ላይ ያለውን ያንብቡ። በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ያሉት ክርስቲያኖች በርካታ ችግሮች ነበሩባቸው። እነዚህ ችግሮች **በመንፈስ ቅዱስ** እንዳይሞሉ አድርገዋቸው ነበር። ለሌሎች ሰዎች ደግ አልነበሩም። እርስ በእርሳቸው የቃላት ጦርነት ውስጥ ውስጥ ይገቡ ነበር። አንዳቸው ለሌላቸው የተሳሳቱ አመለካከቶች ነበሯቸው። ይህ ስለእነርሱ ምን ያሳይ ነበር?

8. 1ኛ ጴጥሮስ 1፥2 ላይ ያለውን ያንብቡ። ***መንፈስ ቅዱስ*** በክርስቲያኖች ውስጥ በተለየ መንገድ ይሠራል። ***መንፈስ ቅዱስ*** ንጹህ እና ጽዱ እንዳንሆን የሚከለክለንን ነገር ያስወግደዋል። ከዚያም እግዚአብሔርን ለማስደሰት እንኖራለን። ጴጥሮስ ይህንን ልዩ ሥራ "**በመንፈስም እንደሚቀደሱ**" ብሎ ይጠራዋል። ኢየሱስ ክርስቶስ ይህ እንዲሆን እንዴት አደረገ?

9. የዮሐንስ ወንጌል 17፥17 ላይ ያንብቡ፡፡

ሀ. ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ  የጸለየው ምን ነበር?

| |
|---|
| ኢየሱስ የጸለየው እግዚአብሔር በእውነት **እንዲቀድሳቸው** ነበር። |

ለ. ኢየሱስ ይህንን ጸሎት ለእርስዎ ጸልዮልዎታል? ይንን ካመኑ፣ ጸሎቱን ይጻፉ ስምዎን ደግሞ በውስጡ ያስገቡ።

10. የሐዋርያት ሥራ 15፥8-9 ላይ ያለውን ያንብቡ። **የተቀደሰ** የሚለው ቃል ከኅጢአት የነጻ ማለት ነው። እግዚአብሔር ለመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ***መንፈስ ቅዱስን*** ሰጥቷቸዋል። ***መንፈስ ቅዱስ*** በምን ነበር ልባቸውን ያነጻው?

11. 1ኛ ተሰሎንቄ 5፥23 ላይ ያለውን ያንብቡ። ይህ ለሁሉም ክርስቲያኖች ያደረገው ጸሎት ነው። ጳውሎስ ለሁሉም ክርስቲያኖች ሁለንተናቸው **እንዲቀደስ** ጸልዮአል። እግዚአብሔር በአጠቃላይ **ይቀድሰናል** ወይም ሙሉ በሙሉ እኛን **ይቀድሰናል** ማለት ነው። በልባችን እና በሕይወታችን ውስጥ ማን ንጹህ ሊያደርገን ይችላል?

12. ጳውሎስ እንዲህ አለ፣ "እንግዲህ፥ ወዳጆች ሆይ፥ የዚህ ተስፋ ቃል ካለን፥ በእግዚአብሔር ፍርሃት ቅድስናን ፍጹም እያደረግን ሥጋንና መንፈስን ከሚያረክስ ሁሉ ራሳችንን እናንጻ።" (2ኛ ቆሮንቶስ 7፥1) ቀጥሎ ካሉት አረፍተ ነገሮች ከጥቅሱ ጋር ማይሔደው የቱ ነው? (ሀ፣ ለ፣ ሐ ወይም መ)

ሀ. ሰውነታችንን የሚጎዱ ነገሮችን ከማድረግ መቆጠብ አለብን።

ለ. በዚህ ሕይወት ውስጥ መቼም ልንነጻ አንችልም።

ሐ. ኢየሱስ ክርስቶስ እንደኖረው ለመኖር መሞከር ይገባናል። በቻልነው ያህል ቅዱሳን ለመሆን መሞከር ይገባናል።

መ. መጥፎ ተግባራትን፣ ሐሳቦችን እና አመለካከቶችን ማስወገድ አለብን።

13. ሮሜ 8፥2 ላይ ያለውን ያንብቡ። የእውነት መንፈስ ህግ ነጻ ያወጣናል። ነጻ የምንወጣው ከምንድን ነው?

14. 1ኛ ቆሮንቶስ 13፥13 ላይ ያለውን ያንብቡ። ክርስቲያኖች እምነት፣ ተስፋ እና ፍቅርን ማሳየት ያስፈልጋቸዋል። ከእነዚህ ከሶስቱ ውስጥ ከሁሉ የሚበልጠው የትኛው ነው?

15. ሮሜ 5፥5 ላይ ያለውን ያንብቡ። የእግዚአብሔር ፍቅር ወደ እኛ የሚመጣው በማን ነው?

16. ሮሜ 8፥4 ላይ ያለውን ያንብቡ። **የተቀደሱ** ክርስቲያኖች ***በመንፈስ ቅዱስ*** ይሞላሉ። አሁን፣ **ኅጢአተኛ ማንነታቸውን** መከተል አይፈልጉም። ከዚያ ይልቅ፣ ከማን ኋላ ለመራመድ ይፈልጋሉ?

ከእንግዲህ፣ **ኀጢአተኛው ማንነት** አኗኗራቸውን አይወስንም። ልባቸው **ነጽቷል**። **መንፈስ ቅዱስ** አዲስ የአኗኗር ዘይቤ ሰጥቷቸዋል። እግዚአብሔርን የሚታዘዙበትን አቅም ሰጥቷቸዋል።

**መንፈስ ቅዱስ** በክርስቲያኖች ውስጥ በብዙ መንገዶች ይሠራል። **የኀጢአተኛ ማንነትን** ልብ ያነጻል። ቅዱስ የሆነ ሕይወት እንዲመሩ ይረዳቸዋል። ለእግዚአብሔር ምስክር እንዲሆኑ ይረዳቸዋል። ነገር ግን መጀመሪያ፣ ክርስቲያኖች አንድ ነገር ማድረግ አለባቸው። **መንፈስ ቅዱስ** ሕይወታቸውን እንዲሞላው መጠየቅ ይገባቸዋል። እራሳቸውን ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር መስጠት ይገባቸዋል።

17. እርስዎ እና መንፈስ ቅዱስ።

ሀ) ለመንፈስ ቅዱስ ሙላት ጠይቀው ነበር? (አዎ ወይም አይ)

ለ) መንፈስ ቅዱስ ሕይወትዎን ሊሞላ መጥቷል? (አዎ ወይም አይ)

ሐ) አይ ካሉ፣ ስለዚህ ነገር እያሰቡ ነው? (አዎ ወይም አይ)

18. **መንፈስ ቅዱስ** ሕይወትዎን እንዲሞላው ይፈልጋሉ? ከፈለጉ፣ ማድረግ ያለብዎ አራት ነገሮች እነሆ፤

- እግዚአብሔር እርስዎን **በመንፈስ ቅዱስ** እንዲሞላዎ ይጠይቁት። (የሉቃስ ወንጌል 11፥13)
- ሁለንተናዎን ለእግዚአብሔር ይስጡ። (ሮሜ 12፥1-2)
- መንጻት እና ከውስጥ መጥራት እንደሚፈልጉ ለእግዚአብሔር ይናገሩ። (የሐዋርያት *ሥራ* 15፥8-9)
- በእምነት **መንፈስ ቅዱስን** ይቀበሉ። እግዚያብሔር **እንደሚቀድስዎ** ይመኑ። ቃል የገባውን ነገር እንደሚያደርግ እርሱን ይመኑ። (1ኛ ተሰሎንቄ 5፥23-24)

*የቃላት ዝርዝር*

1. **ዳግም መወለድ** *(የቅጽል ሐረግ)፡* ክርስቲያንን ወይም አማኝን ይገልጻል፤ ከኀጢአት የዳነ ሰው፣
2. **አማካሪ** *(ስም)፡* ሰዎችን የሚያዳምጥ እና ለችግሮቻቸው መፍትሄ የሚፈልግ ግለሰብ፤ **አማካሪ** *(ተውላጠ ስም)፡* **መንፈስ ቅዱስ**፤ የእግዚአብሔር **መንፈስ**፤ (**መንፈስ ቅዱስ** እንደ **አማካሪያችን** በመሆን በችግሮቻችን ይረዳናል። ለሁሉም ክርስቲያኖች ልዩ ረዳት ነው።)
3. **መንፈስ ቅዱስ፤ የእግዚአብሔር መንፈስ፤ መንፈስ** *(ተውላጠ ስም)፡* ከስላሴ አካላት አንዱ፤ **አማካሪ**፤ ረዳት፤ (እግዚአብሔር ሶስት አካላት አሉት፤ እግዚአብሔር አብ፣ እግዚአብሔር ወልድ፣ እና እግዚአብሔር **መንፈስ ቅዱስ**። **መንፈስ ቅዱስ** በአለም ላይ ያለውን የኢየሱስ ክርስቶስ *ሥራ መሥራቱን* ቀጥሏል። **መንፈስ ቅዱስ** እግዚአብሔርን እንድናውቅ ያበረታታናል እንዲሁም ይረዳናል።)
4. **የነፃ** *(ግስ)፡* ከኀጢአት መጽዳት እና መንጻት፤ በልብ ውስጥ ምንም ኀጢአት አለመኖር፤ (ልባችን እና ሕይወታችን **በመንፈስ ቅዱስ የነፃ** ይሆናል።)

5. **መቀደስ፥ የተቀደሰ** *(ግስ)፡* የነፃ እና ቅዱስ ማድረግ፤ ለኀይማኖታዊ ምክንያት መለየት፤ ከኀጢአት መለየት እና ለእግዚአብሔር መስጠት።

6. **ኀጢአተኛ ማንነት** *(የስም ሐረግ)፡* ኀጢአት እንዲሠራ እና እግዚአብሔርን እንዳይታዘዝ የሚያደርግ የግለሰብ ውስጣዊ ማንነት።

## ትምህርት 8

## ክርስቲያኖች የእግዚአብሔርን ቤተሰብ ይቀላቀላሉ

***በቃል የሚያዝ ጥቅስ፡***

> "በአንዳንዶችም ዘንድ ልማድ እንደ ሆነው፥ መሰብሰባችንን አንተው እርስ በርሳችን እንመካከር እንጂ፤"
> (ዕብራዊያን 10፥25)

ሁሉም ክርስቲያኖች የእግዚአብሔር ቤተሰብ አካል ናቸው። እግዚአብሔር በሰማይ ያለው አባታችን ነው። ክርስቲያኖች በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ እህትማማች እና ወንድማማች ናቸው። ቤተሰቡ **ቤተ ክርስቲያን** ይባላል። እርስዎ ለአዲሱ ቤተሰብዎ ፍቅር ማሳየትዎን አይዘንጉ።

1. መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ ክርስቶስን ስለሚከተሉ ሰዎች ይናገራል። የሐዋርያት ሥራ 11፥26 ላይ ያለውን ያንብቡ። በኢየሱስ የሚያምኑት ሰዎች ምን ይባላሉ?

2. 1ኛ ቆሮንቶስ 12፥27 ላይ ያለውን ያንብቡ። ቤተ ክርስቲያን ምን ተብላ ትጠራለች?

| |
|---|
| የአካላችን ክፍሎች በአንድ ላይ ይሠራሉ። **ቤተ ክርስቲያን** እንደ ክርስቶስ አካል በአንድ ላይ *መሥራት* አለባቸው። |

3. ኤፌሶን 5፥23 ላይ ያለውን ያንብቡ። **የቤተ ክርስቲያን** ራስ ማን ነው?

| |
|---|
| "ራስ" ማለት መሪ ማለት ነው። |

4. ኤፌሶን 5፥25 ላይ ያለውን ያንብቡ። **ቤተ ክርስቲያን** ለኢየሱስ ክርስቶስ አስፈላጊ ነበረች። ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ለምን ሞተ?

5. ኤፌሶን 5፥24 እንደሚለው **ቤተ ክርስቲያን** ለክርስቶስ **ትገዛለች። *መገዛት*** ማለት *መታዘዝ* ማለት ነው። **በቤተ ክርስቲያን** አባል በመሆን፣ ማንን መታዘዝ ይገባኛል?

6. 1ኛ ቆሮንስቶስ 4፥17 ላይ ያለውን ያንብቡ። ጳውሎስ ስለኢየሱስ ያስተማረው የት ነው?

7. የዮሐንስ ወንጌል **ስለቤተ ክርስቲያን** አንዳንድ እውነቶች ይዟል። የዮሐንስ ወንጌል 13፥35 ላይ ያለውን ያንብቡ። እርስዎ **በቤተ ክርስቲያን** ውስጥ መሆንዎን ሰዎች እንዴት ያውቃሉ?

8. የዮሐንስ ወንጌል 21፥16 ላይ ያለውን ያንብቡ። አንድ ***መጋቢ*** ለበጎቹ ምን ማድረግ ይገባዋል?

| |
|---|
| አንዳንድ ጊዜ፣ ***መጋቢውን*** የበጎቹ እረኛ ብለን እንጠራዋለን። ይህ ማለት ***መጋቢው* የቤተ ክርስቲያን** *መሪ* ነው። |

9. ክርስቲያኖች ኢየሱስ ክርስቶስን በተለየ መንገድ ያስታውሱታል። 1ኛ ቆሮንቶስ 11፥23-26 ላይ ያለውን ያንብቡ። እነዚህ ጥቅሶች **ስለጌታ እራት** ይናገራሉ። **የጌታ እራት** ክርስቲያን ለሆኑ ለሁሉም ሰዎች ነው። **ለደህንነታቸው**

ኢየሱስ ክርስቶስን አምነዋል። **ስለጌታ እራት** ልብ ማለት ያለብን ከእነዚህ ውስጥ የትኛውን ነው? (ሀ፣ ለ፣ ሐ ወይም መ)

ሀ) የኢየሱስን ስቃይ እና ሞት እናስታውሳለን።

ለ) ኢየሱስ ለኀጢአታችን እንደሞተ እናስታውሳለን።

ሐ) ኢየሱስ ወደምድር ተመልሶ እንደሚመጣ እናስታውሳለን።

መ) እነዚህን በሙሉ ማስታወስ አለብን (ሁሉንም ሀ፣ ለ አንድ ሐ ማስታወስ ያስፈልጋል)።

10. ገላትያ 6፥2 ላይ ያለውን ያንብቡ። **በቤተ ክርስቲያኔ** ውስጥ ያሉትን ሌሎች ሰዎች እንዴት መርዳት እችላለሁ?

11. 1ኛ ቆሮንቶስ 12፥4 እና 7 ላይ ያለውን ያንብቡ። ለሰዎች ልዩ ልዩ ስጦታዎችን የሚሰጠው ማነው? እንግዲያውስ፣ **በቤተ ክርስቲያን** ውስጥ ያሉ ሁሉም ሰዎች እርዳታውን መቀበል ይችላሉ።

12. አንዳንድ **አብያተ ክርስቲያናት** ጠንካራ እና በፍቅር የታነጹ ናቸው። አንዳንድ **አብያተ ክርስቲያናት** ደግሞ አይደሉም። ከእነዚህ **አብያተ ክርስቲያናት** የትኛውን መቀላቀል ይፈልጋሉ? (ሀ ወይም ለ)

ሀ) በኢየሩሳሌም ያለችው **ቤተ ክርስቲያን**። (የሐዋርያት ሥራ 4፥32-33)

ለ) በሎዶቅያ ያለችው **ቤተ ክርስቲያን**። (የዮሐንስ ራዕይ 3፥14-17)

13. የሐዋርያት ሥራ 2፥42 ላይ ያለውን ያንብቡ። የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ከሐዋርያት ለመማር ጊዜ የሰጡት ነገር ምንድን ነው?

| |
|---|
| እንዲሁም እርስ በእርሳቸው **ኅብረት** ነበራቸው። **እንጀራን የቆረሱት** በጋራ ነው፡፡ |

14. ዕብራውያን 10፥25 ምን ይላል? ይህ ጥቅስ ምን እንድናደርግ ይነግረናል?

| |
|---|
| መሰብሰባችንን መተው የለብንም። እርስ በእርሳችን መበረታታት አለብን። |

15. **ቤተ ክርስቲያንን** መቀላቀል ያለብዎት ይመስልዎታል? (አዎ ወይም አይ) አዎ ካሉ፣ ለምን?

16. እግዚአብሔርን **ለደህንነት** ታምነውታል። እርስዎ አሁን በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ ነዎት። እርስዎ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር **ኅብረት** ፈጥረዋል ወይም ተቀላቅለዋል። በኢየሱስ ክርስቶስ ካሉት ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋርም **ኅብረት** ፈጥረዋል። **ቤተ ክርስቲያንን** ስለመቀላቀል ማሰብ ይኖርብዎታል። ይህ **ኅብረት** ለክርስቲያኖች አስፈላጊ ነው። **ቤተ ክርስቲያንዎ** በአዲሱ እምነትዎ እንዲያድጉ ሊረዳዎ ይችላል። የእርስዎ **መጋቢም** እንዲሁ እንዲያድጉ ሊረዳዎ ይችላል። ከሚከተሉት ውስጥ ስለእርስዎ እውነተኛው ነገር የትኛው ነው? (ሀ፣ ለ ወይም ሐ)

ሀ) ቤተ ክርስቲያንን ተቀላቅያለሁ።

ለ) እስካሁን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አልታቀፍኩም።

ሐ) ቤተ ክርስቲያንን ልቀላቀል እያሰብኩ ነው።

<table><tr><td>
እርስዎ አሁን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትዎን ጨርሰዋል። ከእግዚአብሔር ጋር በሚኖርዎ የወደፊት ጉዞ መልካም ቀኖችን ያያሉ! ያስታውሱ፥<br><br>
• እግዚአብሔርን ይመኑ እና ለእርሱም ይኑሩ።<br><br>
• ቃሉን ያንብቡ እና ከእርሱ ይማሩ።<br><br>
• በጸሎት ከእርሱ ጋር ያውሩ። ይህ የተሰጠዎ ልዩ እድል ነው።<br><br>
• እግዚአብሔርን ያገልግሉ። ራስዎን ለጌታ እና ለሰዎች ይስጡ።<br><br>
• እግዚአብሔር በኢየሱስ ለእርስዎ ስላደረገልዎት ነገር ምስክር ይሁኑ።<br><br>
• አጠቃላይ ሕይወትዎን ለእግዚአብሔር ይስጡ። ከዚያም፣ መንፈስ ቅዱስ ሕይወትዎን እንዲሞላው ይጠይቁት።<br><br>
• **ቤተ ክርስቲያንን** ይቀላቀሉ እና ከአማኞች ጋር **ኅብረት** ያድርጉ።
</td></tr></table>

*የቃላት ዝርዝር*

1. **እንጀራውን መቁረስ** *(የግስ ሐረግ)፡* ምግብ መመገብ፤ **የጌታ እራትም** ተብሎ ይጠራል።

2. **ቤተ ክርስቲያን** *(ተውላጠ ስም)፡* በኢየሱስ ክርስቶስ ያሉ ሁሉም አማኞች፤ ሁሉም ክርስቲያኖች፤ ከኀጢአት የነጹ ግለሰቦች፤ **ለመዳን** እግዚአብሔርን የሚታመኑ ሰዎች።

3. **ቤተ ክርስቲያን** *(ስም)፡* ክርስቲያኖች ለማምለክ የሚገናኙበት ህንጻ ወይም ቦታ፤ የክርስቲያን አማኞች **ኅብረት**።

4. **ኅብረት** *(ስም)፡* ሰዎች ጓደኞች ሲሆኑ እና እርስ በእርስ ሲጋሩ፤ ክርስቲያኖች በኢየሱስ ክርስቶስ **በቤተ ክርስቲያን** ውስጥ ሕይወትን የሚጋሩበት።

5. **የጌታ እራት** *(ተውላጠ ስም ሐረግ)፡* ክርስቲያኖች የኢየሱስን ሞት የሚያስታውሱበት ልዩ ሥርዓት፤ (ክርስቲያኖች ሲሰበሰቡ በተወሰነ ጊዜ **የጌታን እራት** ይጋራሉ። **የጌታ እራት** የጋራ ኅብረትም ተብሎ ይጠራል።)

6. **መጋቢ** *(ስም)፡* **የቤተ ክርስቲያን** ወይም የአማኞች **ኅብረት** መሪ፤ (**መጋቢ በቤተ ክርስቲያን** ውስጥ ያገለግላል። የእግዚአብሔርን ቃል ይሰብካል። ክርስቲያኖች በእምነታቸው እንዲያድጉ ይረዳቸዋል።)

7. **ድነት***(ስም)፡* እግዚአብሔር ሰዎችን ከኀጢአታቸው የሚያድንበት ተግባር።

8. **መገዛት** *(ግስ)፡* ማክበር፣ መስጠት ወይም በሌላ አካል ፈቃድ ስር መሆን።

9. **መተባበር***(ግስ)፡* መቀላቀል፤ **በቤተ ክርስቲያን** ውስጥ አንድ አካል መሆን።

**ማውጫ**

## ለጥያቄዎች ምላሾች

በትምህርቶቹ ውስጥ ላሉት ጥያቄዎች የተጠቆሙ መልሶች እነሆ። በቅንፎቹ ውስጥ መልሶች የሚሆኑ ሌሎች ያገኛሉ። ሌላ ትክክለኛ መልሶችም እንዲሁ ሊያስቡ ይችላሉ።

*ትምህርት 1*

1. አዎ
2. (ሀ) ኢየሱስ (ክርስቶስ)፤ (ለ) እርስዎ (እኔ፣ ማንኛውም ሰው፣ ሁሉም ሰዎች፣ ማንኛዉም ግለሰብ)፤ (ሐ) እንኳን ደህና መጣህ ይበሉት፤ (መ) ይግቡ፤ (ሠ) ግላዊ መልስ
3. አዎ
4. (ሀ) በኀጢአታቸው ምክንያት፤ (ለ) አዎ፤ (ሐ) ግላዊ መልስ
5. ክርስቶስ (ኢየሱስ)
6. እንዲሁ ይቅር ማለት
7. (ሀ)ልክ አይደለም፤ (ለ)ያቁሙ፤ (ሐ) እንዲሁ ይቅር ማለት (ይቅርታ ማድረግ)
8. ሐ (እንዲያድነኝ በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ይገባኛል።)
9. (ሀ) መልካም ሥራዎች፤ (ለ) አይ
10. አባት (አግዚአብሔር፣ እግዚአብሔር አብ)
11. አዎ
12. (ሀ) አዎ፤ (ለ) አዎ፤ (ሐ) ገነት
13. አዎ ወይም አይ - ግላዊ መልስ። አዎ ከሆነ፣ ለምሳሌ፥ “ከኀጢአቴ ንስሐ ገብቻለሁ። ኢየሱስ አዳኜ ነው። ኢየሱስ አድኖኛል።” ሌሎች መልሶችም ይሆናሉ።

*ትምህርት 2*

1. (ሀ) አዎ፤ (ለ) አዎ፤ (ሐ) ኢየሱስ (ክርስቶስ)፤ (መ) አዎ፤ (ሠ) አዎ
2. ዲያብሎስ
3. መፈተን

4. አይ

5. ዲያብሎስን መዋጋት (ከዲያብሎስ በተቃራኒ መቆም፣ ዲያብሎስን አለመታዘዝ፣ እግዚአብሔርን መታዘዝ)

6. የእግዚአብሔርን ህግ መጣስ (ትክክል አለመሥራት፣ እግዚአብሔርን አለመታዘዝ)

7. አዎ

8. (ሀ) ግላዊ መልስ። ለምሳሌ፦ "ኀጢአት መሥራት አይገባኝም (በኀጢአት መቀጠል፣ ኀጢአት እያደረጉ መቀጠል)"፤

1. (ለ) አይ

9. ሀ (እግዚአብሔር ፈተናን እንዳመልጥ ይረዳኛል።)

10. ስለዚህ ኀጢአት አናደርግም።

11. ሐ (ኀጢአትን ለኢየሱስ በመናዘዝ ንስሐ መግባት)

12. አዎ

13. ፍቅር

14. በግ (ክርስቲያኖች፤ አማኞች)

*ትምህርት 3*

1. አዎ

2. አዎ

3. ሁሉም መልሶች "አዎ" ናቸው

4. (ሀ) መጠበቅ (መታዘዝ)፤ (ለ)አዎ፤ (ሐ) መስማት (መቀበል፤ ማመን፤ መታዘዝ፤ ማድረግ)፤ (መ) አዎ፤ (ሠ) እግዚአብሔርን ማክበር (ረ) አዎ

5. አዎ

6. (ሀ) አዎ፤ (ለ) ሕይወት

7. (ሀ) ሰይፍ፤ (ለ) ቃል (ትምህርት)

8. (ሀ) ከመጽሐፍ ቅዱስ ጠቅሷል፤ (ለ) እግዚአብሔር ምን እንደሚፈልግ ይነግሩናል።

9. (ሀ) የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት ይነግረናል፤ (ለ) የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት ማስታወስ

10. ሁሉም ግላዊ መልሶች ናቸው

11. ግላዊ መልስ

12. ግላዊ መልስ። ለምሳሌ፥ በክርስቲያናዊ ሕይወት ለማደግ፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ፣ አሁን እርዳታ ለማግኘት (ሌላ መልሶች ሊሆኑ ይችላሉ)

*ትምህርት 4*

1. ጠዋት (ቀን)

2. ሁልጊዜ

3. ምስጋናን ማቅረብ

4. (ሀ) ኀጢአት (መተላለፍ፤ ክፉት)፤ (ለ) አይ

5. (ሀ) አዎ፤ (ለ) እግዚአብሔር ከሚፈልገው ጋር መስማማት (እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሆነ)

6. (ሀ) ጸሎት፤ (ለ) አዎ፤ (ሐ) አብ፤ (መ) መቆየት (መጣበቅ)

7. ማመን

8. ግላዊ መልሶች

9. ይመልከቱ እና ይጸልዩ

10. ሐ (በልባችን ውስጥ ምን እንደሚሰማን ይንገሩት።)

11. ግላዊ መልሶች

12. ግላዊ መልሶች

*ትምህርት 5*

1. (ሀ) በፍጹም ልቤ፣ ነፍሴ እና ሐሳቤ (ለ) እንደ ራሴ (እኔ)

2. ሁለቱም መታዘዝን ይጠይቃሉ (መከናወን፣ መጠበቅ፤ ማድረግ) የእግዚአብሔር ትእዛዛት

3. (ሀ)መሞት፤ (ለ) ዘላለማዊ (እውነት፣ አዲስ) ሕይወትን አገኛለሁ፤ ክብር

4. የእግዚአብሔር

5. ማንኛውም ነገር፤ ሁሉም ነገር

6. (ሀ) ካሁን በኋላ አለመስረቅ፤ (ለ) መልካም ሠራተኛ መሆን፣ (መ) ከድኾች እና ከሚያስፈልጋቸው ሰዎች ጋር መጋራት

7. ፍቅር፣ ርህራሄ

8. አማኝ ያልሆኑ (በኢየሱስ የማያምኑ ሰዎች)

9. (ሀ) መንፈስ ቅዱስ፤ (ለ) እኔ አሁን የእግዚአብሔር ነኝ።

10. ወንድሞች (እህቶች፣ ሌሎች)

11. አለም

12. ኢየሱስ ትልቅ ዋጋ ከፍሏል (በዋጋ ገዝቶኛል)።

13. (ሀ) የእግዚአብሔር መንግሥት፤ (ለ) የእርሱ ጽድቅ (እግዚአብሔር የሚፈልገው)

14. የዘላለም ሕይወት (ዘላለም የሆነ ሕይወት)

15. ግላዊ መልስ

*ትምህርት 6*

1. ኢየሱስ ለእርሱ ያደረገለት በሙሉ

2. (ሐ) ለራስዎ የሚያዩት እና የሚሰሙት

3. (ሀ) ጴጥሮስ፤ (ለ) እንድርያስ

4. ግላዊ ምላሽ

5. (ሀ) ፍሬ፤ (ለ) ስንመሰክር (ምስክር ስንሆን)

6. ሁሉም ግላዊ መልሶች ናቸው

7. በየትኛውም ቦታ ያሉ ሰዎች በሙሉ (ሌሎች)

8. (ሀ) ሲያምኑ፤ (ለ) ግላዊ መልስ፤ (ሐ) ግላዊ መልስ

9. የሰዎች አጥማጆች

10. መልስ (ምስክርነቴ)

11. ጳውሎስ

12. (ሀ) ምክንያቱም ኢየሱስ መንገድ፣ እውነት እና ሕይወት ነው፤ (ለ) ወደ እግዚአብሔር አብ የሚመራን ኢየሱስ ነው፡፡

13. ረ (እነዚህን በሙሉ መናገር ይገባናል)

14. (ሀ) ግላዊ መልስ፤ (ለ) አዎ፤ (ሐ) አዎ

15. ግላዊ መልስ

16. ግላዊ መላሾች

*ትምህርት 7*

1. መንፈስ ቅዱስ

2. መንፈስ ቅዱስ (አማካሪ፣ ረዳት፣ አጽናኝ)

3. አዎ

4. ኢየሱስ ክርስቶስ

5. ምስክር (ምስክሮች መሆን)

6. አናንያ

7. አለማዊ ነበሩ (ከአለም፤ በአለም እንዳሉ አይነት ሰዎች)

8. በኢየሱስ ደም (ሞት)

9. (ሀ) ራሳቸውን መቀደስ (መለየት)፤ (ለ) ግላዊ መልስ

10. እምነት (በኢየሱስ ያላቸው እምነት)

11. እግዚአብሔር

12. ለ (በዚህ ሕይወት ውስጥ መቼም ልንነጻ አንችልም።)

13. የኀጢአት (ህግ)

14. ፍቅር

15. መንፈስ ቅዱስ

16. መንፈስ (መንፈስ ቅዱስ)

17. ግላዊ መልሶች

18. ግላዊ መልሶች

*ትምህርት 8*

1. ቤተ ክርስቲያን (ሕዝብ)፤ አማኞች (ደቀ መዛሙርት፣ ተከታዮች)፤ ክርስቲያኖች

2. አካል (የክርስቶስ)

3. ክርስቶስ (ኢየሱስ)

4. ሊያድነን

5. ኢየሱስ (እግዚአብሔር)

6. አብያተ ክርስቲያናት

7. ፍቅር (አንዱ ለሌላው ያለው)

8. እንክብካቤ ማድረግ (መምራት)

9. መ (እነዚህን ሶስቱንም ማስታወስ አለብን።)

10. ሸክማቸውን በመሸከም የሚያግዛቸው (ከችግሮቻቸው ጋር)

11. መንፈስ ቅዱስ

12. ሀ (በኢየሩሳሌም ያለችው ቤተ ክርስቲያን ትክክለኛው መልስ ነው።)

13. አስተምህሮ (ዶክትሪን)

14. በአንድ ላይ ለመገናኘት እርስ በእርስ መበረታታት

15. (ግላዊ ምላሾች - ነገር ግን አንዳንድ ጥሩ መልሶች ሊሆኑ ይችላሉ፤ እግዚአብሔርን ማምለክ፤ ከሌሎች አማኞች ጋር ስገናኝ ጠንካራ ሆኜ ማደግ፤ በሌሎች ክርስቲያኖች መታገዝ፤ ስለ እግዚአብሔር የበለጠ መማር)

16. ግላዊ ጥያቄዎች